# የሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ፣አመዘጋገብ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 47/2003

የሕገወጥ ዕቃዎች እንቅስቃሴ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ውስብስብ በመሆኑ እና ውጤታማ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ለመስራት የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ከኮንትሮባንድ፣ ከንግድ ማጭበርበርና ሕገወጥ ዕቃዎች ዝውውር ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በይዘትም ሆነ በመጠን እየተበራከቱና እየተወሳሰቡ በመሄዳቸው በሕጋዊ የንግድ እንቅስቃሴ፣ በመንግሥት ገቢ እንዲሁም በሕብረተሰቡ ደህንነት ላይ አደጋ እያስከተሉ በመምጣታቸው ይህንን ሕገወጥ ድርጊት በተጠናከረ መልኩ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ስልቶችን መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የኮንትሮባንድ እና ሌሎች የጉምሩክ ወንጀሎችን በመከላከል ረገድ መረጃ ወሳኝ በመሆኑና ለዚህም አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ ጠቋሚዎች፣ያዦች፣ ተባባሪዎችና ደጋፊዎች ካደረጉት ተሳትፎ ጋር የተመጣጠነ ወሮታ ሊከፈላቸው የሚገባ በመሆኑ፣

የሕገ ወጥ ዕቃዎች የወሮታ ክፍያ መጠን ለመወሰን፤የወሮታ ክፍያውን ተፈፃሚ ለማድረግ መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ለማስቀመጥ እንዲሁም ሌሎች ከወሮታ ክፍያ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ማካተት በማስፈለጉ፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 78/3/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣አያያዝ እና የወሮታ ክፍያን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 47/2003 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል

1. **"ሕገወጥ ዕቃ"** ማለት የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ ቀረጥ ያልተከፈለበት ወይም ባነስተኛ የተከፈለበት ወይም የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ወይም የኮንትሮባንድ ዕቃ ነው፡፡
2. **"ጥቆማ"** ማለት ለባለሥልጣኑ ወይም ለሕግ አስከባሪ አካል ስለሕገወጥ ዕቃዎች የሚቀርብ መረጃ ነው፡፡
3. **"ጠቋሚ"** ማለት ወሮታ ለማግኘትም ሆነ በሌላ ምክንያት በማናቸውም ሁኔታ ስለሕገወጥ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ለባለሥልጣኑ መረጃ የሚያቀርብ ሰው ነው፡፡
4. **"ያዥ"** ማለት የወሮታ ክፍያ ለማግኘትም ሆነ በሌላ ምክንያት ሕገወጥ ዕቃውን ይዞ ለባለሥልጣኑ ገቢ ያደረገ ሰው ወይም አካል ነው፡፡
5. **"ሠራተኛ"** ማለት የባለሥልጣኑን ሥራ በኃላፊነት እንዲያከናውን የተመደበ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሲሆን የባለሥልጣኑን ሹም ይጨምራል፡፡
6. **"ተባባሪ"** እና **"ድጋፍ ሰጪ"** ማለት ሕገወጡ ዕቃ እንዲያዝ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተሳተፈ ማንኛውም ሰው ነው፡፡
7. **"የወሮታ ክፍያ"** ማለት ለጠቆሙ ወይም ለያዙ ወይም ለተባበሩና ድጋፍ ለሰጡ ሰዎች የሚሰጥ ክፍያ ሲሆን፣ የባለሥልጣኑን ሠራተኛ አይጨምርም፡፡
8. **"ሕግ አስከባሪ"** ማለት በሕግ ማስከበር ተግባር ላይ የተሰማራ የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል የሆነ የታጠቀ ወይም ያልታጠቀ ኃይል ወይም ሠራዊት ነው፡፡
9. **"አዋጅ"** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡
10. **"ባለሥልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡
11. ሌሎች በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሐረጐች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በሕገወጥ ዕቃዎች ላይ የሚቀርቡ ጥቆማዎች አቀራረብ፣ አያያዝ፣ አመዘጋገብ፣ የተያዙ ዕቃዎች ለባለሥልጣኑ ገቢ ስለሚሆኑበት ሁኔታ እና በወሮታ አከፋፈል ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## ስለጥቆማ

### 4. መሠረቱ

በአገሪቱ የጉምሩክ ክልል በየትኛውም ሥፍራ ሕገወጥ ዕቃ መኖሩን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት ወይም ሕግ አስከባሪ አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

### 5. ጥቆማ የማይቀርብባቸው ሁኔታዎች

1. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የሚከተሉት ሁኔታዎች ጥቆማ የማይቀርብባቸው ናቸው፡፡

   ሀ/ በሕዝብ የሚታወቁ ሕገወጥ ዕቃዎች የሚገኙባቸው ቦታዎች፣

   ለ/ ቀደም ሲል በጠቋሚ መረጃ የቀረበባቸው፣

   ሐ/ በአሳማኝ እና በበቂ ማስረጃ ወይም መረጃ ተደግፎ ያልቀረበ ጥቆማ እንደሆነ፤

2. ባለሥልጣኑ ከጠቋሚው የቀረበለትን መረጃ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት ካልተቀበለው ወዲያውኑ ለጠቋሚው በፅሁፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

### 6. የጥቆማ አቀባበል

ባለሥልጣኑ ወይም ሕግ አስከባሪው አካል ሕገወጥ ዕቃ ስለመኖሩ የቀረበለትን መረጃ የሚቀበለው፣

1. ከጠቋሚው በስተቀር በሌላ በማናቸውም ዘዴ መረጃውን ማግኘት የማይችል ከሆነ፣ ወይም፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ "1" የተጠቀሰው ቢኖርም የሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ ቀደም ሲል በባለሥልጣኑ ወይም በሕግ አስከባሪው አካል የሚታወቅ ቢሆንም የቀረበው መረጃ ወይም ማስረጃ ዕቃው የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያመለክት ከሆነ ብቻ ነው፡፡

### 7. የጥቆማ አቀራረብ ዘዴዎች

1. ማንኛውም ጠቋሚ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሕግ አስከባሪ ጥቆማውን በፅሁፍ፣ በቃል፣ በስልክ፣ በፋክስ ወይም በሌሎች ማናቸውም የመገናኛ ዘዴዎች ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ሕግ አስከባሪው ለተቀበለው ጥቆማ ጠቋሚውን በባለሥልጣኑ የወሮታ መቀበያ ቅፅ እንዲመዘገብ የሚያስችል ማስረጃ ሊሰጠው ይገባል፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ቢኖርም በግንባር ሳይቀርብ መረጃ የሰጠ ሰው ባለሥልጣኑ ወይም ሕግ አስከባሪው መረጃውን ወይም ማስረጃው በተቀበለው በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ወደ ባለሥልጣኑ በመቅረብ የጥቆማ መቀበያ ቅፁን የመሙላት ግዴታ አለበት፡፡
3. ነገር ግን ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ በንዑስ አንቀፅ 2 በተገለፀው ቀን መቅረብ ካልቻለ ከአቅም በላይ የሆነበትን ሁኔታ በማስረዳት እስከ ወሮታ ክፍያ መጠየቂያ ጊዜ ቀርቦ ቅፁን መሙላት ይችላል፡፡

## 8. <u>የጥቆማ አመዘጋገብ</u>

1. ማንኛውም ጥቆማ በጥቆማ መቀበያ ቅፅ ላይ እንደቅደም ተከተሉ በጥንቃቄ በኢንተለጀንስ ቡድን ይሞላል፣ ጥቆማውን በግንባር ላቀረበው ሰውም አንዱ ዋና ቅጂ ይሰጣል፡፡ በግልባጭ ለሀብት አስተዳደር፣ ለኦዲትና ኢንስፔክሽን እና ለመረጃ ምርመራና የሥጋት ሥራ አመራር የሥራ ሂደት ያሳውቃል፡፡
2. በጠቋሚነት፣ በያዥነት፣ ድጋፍና ትብብር በማድረግ ሂደት በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች በጋራ ከቀረቡ በጋራ ይመዘገባሉ፡፡
3. ለሕግ አስከባሪ የቀረበ ጥቆማ በ24 ሰዓት ውስጥ ባሉት የመገናኛ ዘዴዎች በአቅራቢያው ለሚገኘው የባለሥልጣኑ መ/ቤት ይተላለፋል፣ በንዑስ አንቀፅ /1/ በተመለከተው መሠረትም ይመዘገባል፡፡
4. የጥቆማ አቀራረብ እና አመዘጋገብን በተመለከተ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው ቅጽ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
5. በንዑስ አንቀፅ /1/ ከተገለፀው ውጪ በሌላ የጥቆማ አቀራረብ ዘዴ የቀረበ ጥቆማ ከሆነ ጠቋሚው በአንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ /2/ ወይም /3/ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ቅፁን እንዲሞላ ተደርጐ ይመዘገባል፡፡ አንዱ ዋና ቅጂም ይሰጠዋል፡፡በግልባጭ በንዑስ አንቀፅ /1/ ለተገለፁት ሦስት የሥራ ሂደቶች ያሳውቃል፡፡

## 9. የጥቆማ ምስጢራዊነት

1. በሕገወጥ ዕቃዎች ላይ የሚደረግ ማንኛውም ጥቆማ እና የጠቋሚው ማንነት አግባብነት ካለው የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ በስተቀር ለማንም ሰው ወይም አካል ምስጢራዊ ሆኖ ይጠበቃል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የጠቋሚውን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ማናቸውም የመረጃ ብክነት እንዳይኖር ከፍተኛ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ እና /2/ ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ ማንኛውም ጥቆማ አስገዳጅ ወይም አሳማኝ ሕጋዊ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ተቋማዊ ይሆናል፡፡
4. ማንኛውም የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ወይም ሕግ አስከባሪ የተቀበለውን ጥቆማ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /3/ ላይ ከተደነገገው ውጪ መረጃውን በፅሁፍ፣ በቃል ወይም በሌላ በማናቸውም ዘዴ ለማንኛውም ሰው አሳልፎ የሰጠ ወይም ምስጢራዊነቱን ያባከነ እንደሆነ አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 10. የጠቋሚ የምስጢር መለያ

ባለሥልጣኑ ማንኛውንም ጠቋሚ የሚለይበት እንዲሁም ከጠቋሚው ጋር ለሚኖረው ማንኛውም ግንኙነት የተለየ ምስጢር መለያ ቁጥር ወይም ስም ለእያንዳንዱ ጠቋሚ ይሰጣል፡፡

## 11. ስለጥቆማ ቅፅ፣ይዘት፣አቀማመጥ እና ስርጭት

በሕገወጥ ዕቃዎች ላይ የሚቀርቡ የጥቆማ መረጃዎች መቀበያ እና መከታተያ ማህደሮች፣ ቅፆች፣ የቅፆቹ ይዘት ዝርዝር እና ብዛት፣ አያያዝ እና አጠባበቅ የመረጃ ምርመራና የሥጋት ሥራ አመራር የስራ ሂደትን ይህን ተግባር ለመፈፀም በሚዘጋጀው ማንዋል መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 12. በባለሥልጣኑ ስለሚመለመሉ ጠቋሚዎች

የሕገወጥ ዕቃ ጠቋሚ አመላመል፣ ሥነ ምግባር፣ ምስጢር አጠባበቅ፣ ሥነ ሥርዓት እና የመረጃ ጥበቃ ስልቶች በሚዘጋጀው ማንዋል መሠረት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ሕገወጥ ዕቃዎች አያያዝ

### 13. ሕገ-ወጥ ዕቃን መያዝና ማስረከብ

1. ባለሥልጣኑ ወይም ሕግ አስከባሪው ሕገወጥ ዕቃ ለመኖሩ ጥቆማ እንደቀረበለት ዕቃውን ወዲያውኑ ይይዛል፡፡
2. ዕቃው በሕግ አስከባሪው የተያዘ እንደሆነ ባለበት ሁኔታ ተመዝግቦ በ48 ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ እንዲተላለፍ እና ርክክብ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡
3. ባለሥልጣኑ የተያዙትን ዕቃዎች በጥንቃቄ መዝግቦ ይረከባል፣ለተረከበው ወይም ለያዘው ዕቃ፣ ሕገወጡን ዕቃ ለያዙ፣ እንዲያዝ ለተባበሩ እና ድጋፍ ላደረጉ ዋናውን ቅጂ ይሰጣል፡፡ በግልባጭ ለሀብት አስተዳደር፣ ለኦዲትና፣ ኢንስፔክሽን እና ለመረጃ ምርመራና የሥጋት ሥራ አመራር የሥራ ሂደት ያሳውቃል፡፡
4. ለዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /3/ አፈፃፀም ለተባባሪዎችና ደጋፊዎች ማስረጃ ለመስጠት ሕገወጡን ዕቃ የያዘው አካል ተባባሪዎቹናደጋፊዎቹ ሕገወጡ ዕቃ እንዲያዝ ተሳትፎ ማድረጋቸውን በመግለፅ ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

### 14. የተያዙ ዕቃዎች አቀማመጥ

1. የተያዙ ዕቃዎች ወዲያውኑ ወደ ባለሥልጣኑ መጋዘን ገቢ ተደርገው ተገቢው አጠባበቅ እና ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የተያዘው ዕቃ በጉምሩክ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጐች መሠረት ለአቀማመጥ ወይም ለአጠባበቅ የማይመች፣ የሚበላሽ ወይም ለሕዝብ ጤና እና ደህንነት አደገኛ ሆኖ ከተገኘ በፎቶግራፍ ወይም በቪዲዮ ምስሉ እንዲቀረጽ ተደርጐ የሚመለከተው ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤት እንዲረከበው ወይም እንዲሸጥ ወይም እንዲወገድ ይደረጋል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /2/ ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ስለተያዘው ሕገወጥ ዕቃ አቀማመጥ፣ አሻሻጥ እና አወጋገድ በተመለከተ በአዋጁ አንቀፅ 31 ንዑስ ቁጥር /8/ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 15. በተያዘ ዕቃ ላይ እንዳይፈፀም የተከለከለ ተግባር

1. ማንኛውም የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ወይም ሕግ አስከባሪ የተያዘን ወይም በቁጥጥር ሥር የዋለን ዕቃ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲውል ማድረግ፣ መሸጥ፣ መለወጥ፣ ማውደም፣ መቀነስ፣ እሽጉ እንዲፈታ ወይም እንዲጠፋ ማድረግ፣ ለአያያዝ እና ለአቀማመጥ እንዳይመች ማድረግ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ሕገወጥ ተግባራትን መፈፀም የለበትም፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተዘረዘረውን በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሞ የተገኘ የባለሥልጣኑ ወይም የሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት
## የወሮታ ክፍያ እና አፈፃፀም

## 16. መሠረቱ

1. ለባለሥልጣኑ በሚቀርብ ጥቆማ ወይም ያለምንም ጥቆማ ሕገወጥ ዕቃ ከተያዘ ጠቋሚው፣ ያዡ፡ ትብብር እና ድጋፍ ያደረጉት በሙሉ በዚህ መመሪያ መሠረት የወሮታ ክፍያ ይከፈላቸዋል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሠረት የወሮታ ክፍያ የሚከፈለው ሕገወጡ ዕቃ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 17 መሠረት የመጨረሻ እልባት ካገኘበት ቀን ጀምሮ በ3 ወር ውስጥ ገቢ የተደረገው ሕገወጥ ዕቃ በቀረጥና ታክስ ወይም በሽያጭ ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ እንዲተላለፉ ወይም እንዲወገድ ቢደረግም ባይደረግም ክፍያው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
3. ቀረጥና ታክስ ሊሰራላቸው ከማይችሉ ሕገወጥ ዕቃዎች በስተቀር የተያዘው ሕገወጥ ዕቃ ከተሸጠ ወይም ከተላለፈ ወይም በማንኛውም መንገድ ከተወገደ ለወሮታ ክፍያው መሠረት የሚሆነው በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ ሲሆን መቀጫውን አይጨምርም፡፡

4. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8/1/፣ 8/5/ እና 13/3/ መሠረት ጠቋሚ፣ ያዥ፣ ደጋፊ እና ተባባሪ ለመሆኑ ከባለሥልጣኑ ማስረጃ የተሰጠው ሰው የክፍያ ጥያቄ በሚያቀርብበት ወቅት የተሰጠውን ማስረጃ ዋና ቅጂ ይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

17. <u>ሕገወጥ ዕቃ ለባለሥልጣኑ ገቢ ሆኗል ስለሚባልበት ሁኔታ</u>

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል ሕገወጥ ዕቃ ለባለሥልጣኑ ገቢ እንደተደረገ የሚቆጠረው፣

1. የተከለከለ ዕቃ ከሆነ በባለሥልጣኑ እንደተያዘ ወይም ባለሥልጣኑ እንደተረከበው ወይም
2. ለተያዘው ዕቃ ባለቤት ወይም ኃላፊ የሆነ ሰው ማስታወቂያ በወጣ በ30 ቀናት ውስጥ ካልቀረበ ወይም በዚሁ ጊዜ ውስጥ በፍ/ቤት ክስ ካልመሰረተ በዕቃው ላይ የሚኖረው መብት ተቋርጦ ዕቃው በአዋጁ አንቀፅ 31 መሠረት ሲወገድ፤ወይም
3. በሕገወጡ ዕቃ ባለቤት፣ በግብረ አበሮቹ እና/ወይም በተባባሪዎቹ ላይ ባሉበትም ሆነ በሌሉበት በቀረበባቸው የወንጀል ክስ መሠረት ሥልጣን በተሰጠው ፍ/ቤት በዕቃው ወይም በወንጀለኛው ላይ የመጨረሻ የውርስ ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲሰጥ ወይም፤
4. ተከሳሹ ፍርድ ቤት ባለመቅረቡ ምክንያት ክስ የማቅረብ መብት ተጠብቆ በተዘጋ ክስ ላይ ፍርድ ቤት ሕገወጥ ዕቃው ተሸጦ ለባለሥልጣኑ ገቢ እንዲሆን ትእዛዝ ሲሰጥ፣ ወይም ባለሥልጣኑ ሕገወጡ ዕቃ በአስተዳደራዊ ውሳኔ አስፈላጊውን ክፍያ ተከፍሎ እንዲወጣ ሲወስን፤ወይም
5. ቀረጥና ታክስ ማሳነስ ወይም ማጭበርበር በተፈፀመበት ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ እንዲሁም መቀጫ ሲሰበሰብ ሕገወጡ ዕቃ ገቢ ሆኗል ይባላል፡፡

18. <u>የወሮታ ክፍያ መጠን</u>

1. በቀረጥ ነፃ ወይም በጊዜያዊነት ወይም በሕገወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ ገብተው መብቱ በሌላቸው ግለሰቦች ወይም ግለሰብ ይዞታ ሥር ሆኖ የተያዘን ዕቃ በተመለከተ የሚከፈለው የወሮታ መጠን ዕቃው በተላለፈበት ጊዜ ወይም ዕቃው የተላለፈበት ጊዜ በትክክል ማወቅ የማይቻል ሲሆን ዕቃው ወደ አገር ውስጥ በገባ ጊዜ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ላይ፣

ሀ/ ለጠቋሚ 15%

ለ/ ለያዥ፣ድጋፍናትብብር ላደረጉ 10%

ሐ/ ዕቃው የተያዘው በክልል ወይም በከተማ መስተዳድር አካላት ወይም በመከላከያ ሠራዊት ወይም በፌዴራል ፓሊስ ሲሆን ለተቋሙ 50% የወሮታ ክፍያ ይከፈላል፡፡

መ/ ለዚሁ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ /ሐ/ አፈፃፀም ለሕግ አስከባሪ ጥቆማ ያቀረበው ግለሰብ ከሆነ ለህግ አስከባሪ ከሚከፈለው 50% ክፍያ ላይ በንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ የተመለከተው ተቀናሽ ተደርጐ ለጠቋሚው ይከፈለዋል፡፡

2. ማንኛውም ሰው መከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዳይከፈል ወይም አሳንሶ ለመክፈል ወይም ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ለማድረግ በማናቸውም ሁኔታ ማጭበርበር መፈፀሙን ተጠቁሞ በምርመራ የተገኘ እንደሆነ ማጭበርበር ወይም ማሳሳት በተፈፀመበት ሕገወጥ ዕቃ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ላይ፤

ሀ/ ለጠቋሚ15%

ለ/ ለያዥ፤ድጋፍናትብብር ላደረጉ 10% የወሮታ ክፍያ ይከፈላል፡፡

3. ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው የባለሥልጣኑ ሹም ፈቃድ ሳያገኝ አስፈላጊውን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት በመፈፀም ወደ ውጭ ሀገር እንዲወጣ ወይም ወደሀገር ውስጥ እንዲገባ ወይም እንዲተላለፉ በተፈቀደ ማጓጓዣ ወይም የዕቃ መያዣ ላይ የተደረገውን ማሸጊያ በመፍታት ወይም መያዣውን ከፍቶ ወይም ሰብሮ ዕቃውን ማጉደሉ ጥቆማ ደርሶ የተያዘ እንደሆነ በተቀነሰው ዕቃ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ፤

ሀ/ ለጠቋሚ 20%

ለ/ ለያዥ፣ ተባባሪና ደጋፊ 10%

ሐ/ ለክልል ወይም ለከተማ መስተዳድር አካላት ወይም ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፌዴራል ፓሊስ 40%

መ/ ለዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ /ሐ/ አፈፃፀም ለህግ አስከባሪ ጥቆማ ያቀረበው ግለሰብ ከሆነ ለህግ አስከባሪው ከሚከፈለው 40% ክፍያ ላይ በንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ የተመለከተው ተቀናሽ ተደርጐ ለጠቋሚው ይከፈለዋል፡፡

4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /3/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የተቀነሰው ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሊሠራለት የማይችል ሲሆን የተቀነሰው ዕቃ በሚመለከተው መስሪያ ቤት የገበያ ዋጋ የወጣለት ከሆነ የዚሁ ዋጋ የሚወሰድ ሲሆን የገበያ ዋጋ የማይወጣለት

ከሆነ ባለስልጣኑ በሚሰይመው ከ3 ያላነሱ የቡድን አባላት እንደየ ዕቃው ባህሪ እየተጣራ ከሚሰጠው ዋጋ ላይ በንኡስ አንቀፅ /3/ ለጠቋሚ፣ ለያዥ፣ ለተባባሪና ደጋፊ እንዲሁም ለክልል ወይም ለመስተዳድር አካላት ወይም ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፌዴራል ፓሊስ የተገለፀውን ክፍያ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5. ሽያጭ ላይ የማይውሉ ሕገወጥ እቃዎች የወሮታ ክፍያ መጠን፤

የተያዘው ዕቃ ቅርሳ ቅርስ፣ በሕግ የተከለከሉ የዱር አንስሳት ተዋጽኦዎች፣ የጦር መሳሪያ፣ ፈንጂ ፣ተቀጣጣይ፣ ወይም መርዛማ ኬሚካል እና ዝቃጮች፣ ትምባሆ፣ መድሀኒቶች፣ ልባሽ ጨርቅ እና ሌሎች በሽያጭ ሊወገዱ የማይችሉ ዕቃዎች የሆኑ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ለጠቋሚ፣ ያዥ፣ ድጋፍና ትብብር ላደረጉ ሰዎች እንደሚከተለው ክፍያ ይፈፀማል፡-

1. ሕገወጥ ዕቃው ልባሽ ጨርቅ ከሆነ የወሮታ ክፍያ መጠኑ በኪሎ ብር 25 እንዲታሰብ ተደርጐ፤

   ሀ/ 25% ለጠቋሚ፣

   ለ/ 15 %ለያዥ፣ ድጋፍና ትብብር ላደረጉ፣

   ሐ/50% ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለክልል ወይም ለከተማ መስተዳድር አካላት ወይም ለፌዴራል ፓሊስ ይከፋፈላል፡፡

2. ሕገወጥ ዕቃው በሚመለከተው መስሪያ ቤት ዋጋ የወጣለት ከሆኑ የዚህኑ ዋጋ፤

   ሀ/ ለጠቋሚ 20%፣

   ለ/ ለያዥ ድጋፍና ትብብር ላደረጉ 15%፣

   ሐ/ ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፌዴራል ፓሊስ ወይም ለክልል ወይም ለከተማ መስተዳድር አካላት 40% ይከፈላል፡፡

3. ሕገወጥ ዕቃው የገበያ ዋጋ ሊወጣለት የማይችል ከሆነ ባለሥልጣኑ በሚሰይመው ከ3 ያላነሱ አባላት ያሉት ቡድን አማካኝነት እንደየእቃው ባህሪ እየተጣራ ቡድኑ ለዕቃው ከሚሰጠው ዋጋ ላይ፤

   ሀ/ ለጠቋሚ 10%፣

   ለ/ ለያዥ፣ ድጋፍናትብብር ላደረጉ 5%፣

   ሐ/ለመከላከያ ሰራዊት ወይም ለፌዴራል ፓሊስ ወይም ለክልል ወይም ለከተማ መስተዳድር አካላት 30% ይከፈላል፡፡

4. ለዚሁ ንዑስ አንቀፅ ተራ ቁጥር 1፣2፣ እና 3 አፈፃፀም ለሕግ አስከባሪ ጥቆማ ያቀረበው ግለሰብ ከሆነ ለሕግ አስከባሪው ከሚከፈለው፤ብር 50፣ 40%,፣ 30% ክፍያ ላይ በንዑስ አንቀፅ 5/1/፣/2/ እና /3/ እንደቅደም ተከተሉ ለጠቋሚ የተመለከተው ተቀናሽ ተደርጐ ለጠቋሚው ይከፈለዋል፡፡

6. የተያዘው ሕገወጥ ዕቃ የውጭ አገር ገንዘብ ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ ብር ከተመነዘረ በኋላ፤

ሀ/ ለያዥ የ15%

ለ/ ለጠቋሚ 10%

ሐ/ ትብብር እና ድጋፍ ለሚያደርጉ 5%

መ/ ዕቃው የተያዘው በመከላከያ ሠራዊት ወይም በፌዴራል ፓሊስ ወይም በክልል ወይም በከተማ መስተዳድር አካላት ሲሆን 30%

ሠ/ ለዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ /መ/ አፈፃፀም ለህግ አስከባሪ ጥቆማ ያቀረበው ግለሰብ ከሆነ ለተቋሙ ከሚከፈለው 30% ክፍያ ላይ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (ለ) የተመለከተው ተቀናሽ ተደርጐ ለጠቋሚው ይከፈላል፡፡

7. የተያዘው ሕገወጥ ዕቃ የኢትዮጵያ ብር ከሆነ፣

ሀ/ ለያዥ 20%

ለ/ ለጠቋሚ 15%

ሐ/ ትብብር እና ድጋፍ ላደረጉ 5%

መ/ ዕቃው የተያዘው በመከላከያ ሠራዊት ወይም በፌዴራል ፓሊስ ወይም በክልል ወይም በከተማ መስተዳድር አካላት ሲሆን 35%

ሠ/ ለዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ /መ/ አፈፃፀም ለሕግ አስከባሪ ጥቆማ ያቀረበው ግለሰብ ከሆነ ለሕግ አስከባሪ ከሚከፈለው 35% ክፍያ ላይ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ /ለ/ የተመለከተው ተቀናሽ ተደርጐ ለጠቋሚው ይከፈላል፡፡

8. ሕገወጡን ዕቃ ለያዙ፣ ለተባበሩና ድጋፍ ላደረጉ ለክልል ወይም ለከተማ መስተዳድር አካላት ወይም ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፌዴራል ፓሊስ አባላት እንደየዕቃው ባህሪ በመመሪያው ለያዥ የተመለከተው ክፍያ ለክልል ወይም ለከተማ መስተዳድር አካላት ወይም ለፌዴራል ፓሊስ ወይም ለመከላከያ ሠራዊት ከሚከፈለው ላይ ተቀናሽ ተደርጎ ይከፈላቸዋል፡፡

9. የተያዘው ሕገወጥ ዕቃ ሲሸጥ ወይም ቀረጥና ታክስ ተከፍሎ ሲወጣ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ሲወገድ ሽያጩን ለማከናወን የወጣውን ወጪ የመጋዘን ኪራይ እና ዕቃውን ለማጓጓዝ የወጣው ወጪ ከተቀነሰ በኋላ በቀሪው ሂሳብ ላይ የወሮታ ክፍያ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

10. በጠቋሚ፣በያዥ፣ ድጋፍና ትብብር በማድረግ ሂደት በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች በጋራ ከጠቆሙ፣ከያዙ፣ድጋፍና ትብብር ካደረጉ የወሮታ ክፍያው እንደየድርሻቸው ተፈፃሚ ይደረግላቸዋል፡፡

## 19. የወሮታ ክፍያ ፈፃሚ ሊያከናውናቸሉ የሚገቡ ተግባሮች

1. የሀብት አስተዳደር ወይም ፋይናንስ እንደየጉዳዩ አግባብነት የሚከተሉትን ማስረጃዎች ሊያሰባስብ ይገባል፡-

   ሀ/ በአንቀፅ 8/1/፣8/5/ እና 13/3/ መሠረት ለጠቋሚ፣ለያዥ እና ትብብርናድጋፍ ላደረጉት ማስረጃ ሲሰጣቸው በወቅቱ ለሀብት አስተዳደር /ፋይናንስ ቡድን/፣ ለኦዲት እና ኢንስፔክሽን /ኦዲት ቡድን/፣ለመረጃ ምርመራናሥጋት ሥራ አመራር የስራ ሂደት /ለህግ ማስከበር/ በግልባጭ የደረሰ መሆኑን፣

   ለ/ ሕገወጥ ዕቃው ወደ መጋዘን ገቢ የተደረገበት ደረሰኝ፣

   ሐ/ ዕቃው ወጪ ሆኖ ገዥው የተረከበበት ደረሰኝ፣

   መ/ ዕቃው የተሸጠበት ደረሰኝ፣

   ሠ/ ጠቋሚ፣ያዥ፣ተባባሪናደጋፊ ለመሆኑ በባለሥልጣኑ የተሰጠውን ማስረጃ ዋና ቅጅ መቀበልና ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ፣

   ረ/ የአስተዳደራዊ ውሳኔ ደብዳቤ፣

   ሰ/ የዕቃው ዲ/ዮን፣

   ሸ/ ልዩነት የተከፈለበት ደረሰኝ፣

   ቀ/ የልዩነት ፎርም፣

   በ/ በደንብ መተላለፍ የልዩነት ዋጋ የተሠራበት ቅፅ፣

   ተ/ ሽያጭ ላይ የማይውሉ ሕገወጥ ዕቃዎች ሲሆኑ በዕቃ አወጋገድ መመሪያ የተያዘው ቃለ ጉባኤ መሟላቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ እንደተጠበቀ ሆኖ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ሥርዓት መሠረት የተገኘ የማጭበርበር ድርጊት በሆነ ጊዜ የቀረጥና ታክስ እና መቀጫ መከፈሉን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 20. የወሮታ ክፍያ መብት የሚተላለፍ ስለመሆኑ

ጠቋሚ፣ያዥ፣ድጋፍናትብብር አድራጊው የወሮታው ክፍያ ሳይፈፀምለት ቢሞት ወይም ቢጠፋ መብቱ ሕግ ለሚፈቅድላቸው ባለመብት ይተላለፋል፡፡

### 21. የይርጋ ጊዜ

1. ሕገ ወጡ ዕቃ ለባለሥልጣኑ ገቢ ከሆነበት ከሦስተኛው ወር ጊዜ ጀምሮ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ የክፍያ ጥያቄ ካልቀረበ መብቱ በይርጋ ይታገዳል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም የክፍያ ጥያቄው የዘገየው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት እንደሆነ፣ ከዐቅም በላይ የሆነው ሁኔታ ከተወገደ በኋላ አሳማኝ ማስረጃ ሲቀርብለት ባለሥልጣኑ የጊዜ ገደቡን ለተጨማሪ 6 ወራት ሊያራዝም ይችላል፡፡

### 22. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን በፊት የነበሩ ጉዳዮች በሙሉ ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ሥራ ላይ የነበረው መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### 23. የተሻረ መመሪያ

የሕገወጥ እቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 15/2001 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 24. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ-------------------ቀን 2003 ዓ.ም**

**መላኩ ፈንታ**

**የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**

# የሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ፣ አመዘጋገብ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን  የቀረበው ረቂቅ መመሪያ ማብራሪያ

## ሀ. መግቢያ

መመሪያውን እንደገና ማውጣት ያስፈለገበት ምክንያት ተጨምሯል፡፡

የሕገወጥ ዕቃዎች የወሮታ ክፍያ መጠን ለመወሰን፣ የወሮታ ክፍያውን ተፈፃሚ ለማድረግ መሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ለማስቀመጥ እንዲሁም ሌሎች ከወሮታ ክፍያ ጋር የተያያዙ  ዝርዝር ጉዳዮችን ማካተት በማስፈለጉ፤

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   አልተሻሻለም

2. **ትርጓሜ**

2(1) ፣ 2/2/፣ 2/3/፣ 2/4/፣ 2/5/፣ 2/7/፣ 2/8/ ተሻሽለዋል፡፡ 2/11/ አዲስ ንዑስ አንቀፅ ተጨምሯል፡፡

1. "ሕገወጥ ዕቃ"

   በአዋጁ አንቀፅ 78/1/ የተዘረዘሩት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ለመመሪያው መውጣት መነሻ የሆነው የአዋጁ አንቀፅ 78 ውስጥ የወሮታ ክፍያ መሠረት የሚያደርገው መንግሥት ሊያጣው ይችል የነበረውን ቀረጥና ታክስ ገቢ ማድረግን በተመለከተ ሲሆን ቅርስን ወይም የህብረተሰቡን ደህንነት እንዲሁም የሀገሪቱን ጥቅም ከመጠበቅ ወይም ከማስጠበቅ አንፃር ትኩረት በመስጠት ነው፡፡ክፍያውም መሠረት የሚያደርገው በተያዘው ዕቃ ላይ ከሚሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ወይም ሽያጭ ወዘተ የሚገኘውን ገቢ መሠረት በማድረግ ነው፡፡በተጨማሪም የተከለከሉ እቃዎችን በተመለከተ መንግስት ለዚሁ አላማ በሚይዘው በጀት መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. **"ጥቆማ"** ማለት

አልተሻሻለም

3. **"ጠቋሚ"** እና 4. **"ያዥ"** ማለት ተሻሽሏል፡፡

የወሮታ ክፍያ ለማግኘት ብቻ ሳይሆን "በሌላ ምክንያት" በማናቸውም ሁኔታ ስለሕገወጥ ዕቃዎች እንቅስቃሴ መረጃ የመስጠት፣ ወይም መያዝ በማንኛውም ሰው የተጣለ ግዴታ በመሆኑ፣ ለማግኘት ብቻ አለመሆኑን እንዲጨመር ተደርጓል፡፡

5. **"ሠራተኛ"** ማለት

የባለሥልጣኑን ሥራ በኃላፊነት እንዲያከናውን የተመደበ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሲሆን የባለሥልጣኑ ሹም ይጨምራል በሚል ተሻሽሎ ተተርጉሟል፡፡

6. **"ተባባሪና ድጋፍ ሰጪ"** ማለት

አልተሻሻለም

7. **"የወሮታ ክፍያ"** ማለት

ለጠቆሙ ወይም ለያዙ ወይም ለተባበሩና ድጋፍ ለሰጡ ሰዎች የሚሰጥ ክፍያ ሲሆን የባለሥልጣኑ ሠራተኛ አይጨምርም በሚል ተስተካክሏል፡፡ የፌዴራል ፓሊስ አይጨምርም የሚለው ወጥቷል፡፡ ምክንያቱም ከመከላከያ ሠራዊት፣ ከክልል ወይም ከከተማ አስተዳደር የተለየ ተግባር የሌለው በመሆኑ እና ሊከሰቱ ይችላሉ ተብሎ የሚገመቱ ችግሮችን ለመቅረፍናሕገወጥ ዕቃዎች በተፋጠነ ሁኔታ እንዲያዙ ለማበረታታት ሲባል ነው፡፡

8፣9 እና 10 አልተሻሻሉም፡፡

11. አዲስ ንዑስ አንቀፅ ተጨምሯል

በመመሪያው ያልተካተቱ /ያልተተረጐሙ የሕግ ፍሬ ነገሮች ሲያጋጥሙ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 የተሰጠ ትርጓሜ ለዚሁ መመሪያ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

**አንቀፅ 3 የተፈፃሚት ወሰን**

አመዘጋገብ የሚል ቃል እንዲገባ ተደርጓል ምክንያቱም መመሪያው የተያዘው ሕገወጥ ዕቃ እንዴት ይመዘገባል የሚለውን ማካተት ስለሚኖርበት፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለጥቆማ</u>

**አንቀፅ 4 <u>መሠረቱ</u>**

አልተሻሻለም

**አንቀፅ 5 <u>ጥቆማ የማይቀርብባቸው ሁኔታዎች</u>**

አልተሻሻለም

**አንቀፅ 6 <u>የጥቆማ አቀባበል</u>**

1. በ "ሀ" እና "ለ" ተከፍለው የነበሩ 1 እና 2 እንዲሆን ተደርጓል፡፡
2. በቀድሞ ፊደል ተራ "ሀ" የነበረበአሁኑ "1" ሆኖ "የማይቻል" ይል የነበረው የማይችል በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

**አንቀፅ 7 የጥቆማ አቀራረብ ዘዴዎች**

**የተሻሻለ ሲሆን አዲስ ንዑስ አንቀፅ /2/ ተጨምሮበታል**

1. ማንኛውም ጠቋሚ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሕግ አስከባሪ ጥቆማው በፅሁፍ፣ በቃል በስልክ፣ በፋክስ ወይም በሌሎች ማናቸውም የመገናኛ ዘዴዎች ሊያቀርብ እንደሚችል ሆኖም ለሕግ ማስከበር የቀረበው ጥቆማ በተመለከተ ህግ አስከባሪው ጥቆማውን እንደተቀበለ ጠቋሚው ጥቆማ ለማቅረቡ የሚያሳይ እና ወደ ባለሥልጣኑ በግንባር በመቅረብ ለወሮታ ክፍያ የሚያበቃውን ቅፅ እንዲሞላ ይረዳው ዘንድ ከህግ አስከባሪው ማስረጃ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ይህም ጥቆማውን ለጠቆመው ግለሰብ ጥቅም ሲባል እንዲገባ ተደርጓል፡፡
2. ንዑስ አንቀፅ /1/ ቢኖርም በግንባር ሳይቀርብ መረጃ የሰጠ ሰው በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ወደ ባለሥልጣኑ በመቅረብ የጥቆማ መቀበያ ቅፅ የመሙላት ግዴታ አለበት፡፡ ጥቆማው ለባለሥልጣኑ ሲቀርብ ሲባል ጥቆማ የሚቀበለው የመረጃ ምርመራና ስጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ሥር ላለው የኢንተለጀንስ ቡድን መሆኑን የሚታወቅ ነው፡፡

ንዑስ አንቀፅ /2/ እንዲገባ የተደረገበት ምክንያት በስልክ፣በኢሜል፣በፓስታ ወዘተ ጥቆማ ለሚያቀርቡ ሰዎች በግንባር ቀርበው ኦርጅናል ቅፁን መውሰድ እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱም ኦሪጅናል ቅፅ ካልያዙ የወሮታ ክፍያ ስለማይፈፀምላቸው በንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ተብሎ የገባው ጠቋሚው በደረሰበት ችግር ምክንያት በተወሰነው ጊዜ ቀርቦ ጥቆማውን እንዳይሰጥ እንቅፋት ሊሆን የሚችል እና ጠቋሚው ሊያስወግደውም ሆነ አስቀድሞ ሊገምተው የማይችለው ሁኔታ ሲሆን የወሮታ ተከፋይነቱን እንዳያጣ ለማድረግ ሲባል ነው፡፡ይህም በተፈጠረ ጊዜ ሁኔታዎቹ ለመፈጠራቸው የሚያሳይ ማስረጃ ይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ሕግ አስከባሪው ከአባሉ ወይም በአቅራቢያው ባለው ሰው የተሰጠውን መረጃ መሠረት በማድረግ ዕቃው ባለበት ሁኔታ በፍጥነት መያዝ እንዲችል እና ባለሥልጣኑ በፍጥነት ሊደርስበት የማይችለውን ሁኔታ በመቆጣጠር ሕገወጡን ዕቃ ይይዝ ዘንድ ከመረጃ አቅራቢዎች ጥቆማውን እንዲቀበል ሆኖ በተቀበል በ24 ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ የመረጃ ምርመራና የሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት መረጃውን በማቅረብ ህገወጡን ዕቃ መያዝ እና በ48 ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ እንሚያስረክብ ተገለፀ፡፡ የኢንተለጀንስ ቡድንም ጥቆማው እንደደረሰው በግልባጭ ከላይ ለተጠቀሱት ለሦስቱ የሥራ ሂደቶች ያሳውቃል፡፡ በቅ/ጽ/ቤቶችም ቢሆን ጥቆማው ለመረጃ ቡድኑ ሲደርስ በቅ/ጽ/ቤቱ ላሉት የፋይናንስ፣ ኦዲት እና ለሕግ ማስከበር ያሳውቃሉ፡፡

የመረጃ ንዑስ የሥራ ሂደት የሚለው ወጥቶ ባለሥልጣኑ በሚል ተሻሽሏል፡፡ ምክንያቱም የባለሥልጣኑን የሥራ ሂደቶች አደረጃጀት ለውጥ ሲደረግባቸው የሚመለከተውን የሥራ ሂደት ለማስገባት ሲባል መመሪያውን በየጊዜው እንዲሻሻል የሚያደርግበትን ሁኔታ ለማስወገድ ሲባል የተቀየረ ነው፡፡

**አንቀፅ 8 <u>የጥቆማ አመዘጋገብ</u>**

**ተሻሽሏል**

1) የጥቆማ መቀበያ ቅጽ ማስረጃ ለጠቋሚ ሲሰጥ በግልባጭ ለሚመለከተው ሦስት የሥራ ሂደት በወቅቱ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፤ ይህ የተደረገበት ምክንያት ቅጹው /ማስረጃው ቢጠፋ፣ ጠቋሚው ቢሞት የወሮታ አከፋፈሉ ችግር እንዳይፈጠር ግልባጩ በሌሎች የሥራ ሂደቶች እንዲገኝ ለማድረግ፤ በሌላ በኩል በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ወይም

በኃላፊዎች መቀያየር ወይም ባለመብቱ ባለመቅረቡ በሌላ ሰው ስም ለክፍያ ሲቀርብ፣ ወይም ተከፍሎ ቢገኝ ለመቆጣጠር እንዲመች ለማድረግ ነው፡፡

2) ጠቋሚ፣ ያዥ፣ ደጋፊና ትብብር በማድረግ በጋራ በአንድ ጊዜ ከመጡ በጋራ እንዲመዘገቡ፣
3) አሁን ባለንበት የቴክኖሎጂ ዘመን በማንኛውም መገናኛ መንገድ ማስተላለፍ የሚቻል በመሆኑ 48 ሰዓት ብዙ ሰዓት ስለሆነ በ24 ሰዓት መረጃው ይቀርብ ዘንድ ተስተካክሏል፣
4) ባለሥልጣኑም መረጃ አቀባበል፣ አመዘጋገብ፣ አያያዝ በሚመለከት በአንድ ወጥ የሆነ ቅጽ/አሠራር እንዲጠቀም አዲስ ንዑስ አንቀፅ ተጨምሯል፣
5) በንዑስ አንቀፅ /1/ ከተገለፀው ውጭ በሌላ አካኋን የጥቆማ አቀራረብ ዘዴ የቀረበ ጥቆማ ከሆነ በአንቀፅ 7/2/ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ቅፁን እንዲሞላ ተደርጐ ይመዘገባል፡፡ ከፍ ብለው ለተጠቀሱት 3 የሥራ ሂደቶች በግልባጭ እንዲያውቁት ይደረጋል የሚል ተጨምሯል፡፡

**አንቀፅ 9 <u>የጥቆማ ሚስጢራዊነት</u>**

ከንዑስ አንቀፅ 1-3 አልተሻሻለም

ንዑስ አንቀፅ 4 ተጠያቂነቱ ለባለሥልጣኑ ሠራተኛ/ ኃላፊ ብቻ የነበረ ተጠያቂነት ለሕግ አስከባሪ አካላትም እንደሚጨምር፤ በወንጀል ሕግ መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ በዲሲፕሊን እንዲከሰስ ይደረጋል የሚለውን "አግባብ ባለው ሕግ" ተጠያቂ ይሆናል በሚል ተለውጧል፡፡ እንዲሁም ለሀብት አስተዳደር፣ ለኦዲትና ኢንስፔክሽን እና ለመረጃ ምርመራና የሥጋት ሥራ አመራር የሥራ ሂደት በግልባጭ እንዲያውቁት መደረጉ ሚስጢሪዊነቱን አያሳጣውም ወይ የሚል ሀሳብ ሊነሳ ይችላል፡፡ ሆኖም ለነዚህ የሥራ ሂደቶች ግልባጭ የሚደረግበት እና የጠቋሚውን ሙሉ ማንነት የሚመዘገብበት መዝገብ የተለያየ በመሆኑ ሚስጥራዊነቱን የሚያሳጣውን ሁኔታ ይቀርፈዋል፡፡

**አንቀፅ 10 <u>የጠቋሚ የሚስጥር መለያ</u>**

አልተሻሻለም

አንቀፅ 11 **<u>ስለጥቆማ ቅጽ፣ይዘት፣ አቀማመጥ እና ሥርጭት</u>**

የመረጃ ንዑስ የሥራ ሂደት የሚለውን የመረጃ ምርመራና የሥጋት ሥራ አመራር የሥራ ሂደት እንዲሆንና በተዘጋጀው ማኑዋል የሚለው "በሚዘጋጀው ማኑዋል" መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

**አንቀፅ 12** <u>በባለሥልጣኑ ስለሚመለመሉ ጠቋሚዎች</u>

"በተዘጋጀው ማኑዋል" የሚለውን "በሚዘጋጀው ማንዋል" እንዲተካ ተደርጓል፡፡

በአንቀፅ 11 እና 12 "በሚዘጋጀው ማኑዋል" እንዲስተካከል የተደረገው በአሁኑ ወቅት የተዘጋጀ ማንዋል ባለመኖሩም ነው፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለህገወጥ ዕቃዎች አያያዝ</u>

**አንቀፅ 13** <u>ሕገወጥ ዕቃን መያዝና ማስከረብ</u>

1. አልተሻሻለም
2. መመሪያ ቁጥር 15/2001 በ24 ሰዓት ይል የነበረው በ48 ሰዓት፣ በሕግ አስከባሪ የተያዘው ሕገወጥ ዕቃ ለባለሥልጣኑ እንዲተላለፍና ርክክብ እንዲፈፀም ይደረጋል በሚል እንዲተካ ተደርጓል፡፡ ይህም በ24 ሰዓት ውስጥ ማስረከብ የማይቻልበት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ከባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ርቀት አንፃር ነው፡፡
3. በባለሥልጣኑ የተያዙትን ዕቃዎች በጥንቃቄ መዝግቦ ይረከባል ለተረከበው ወይም ለያዘው ዕቃ፣ ሕገወጥን ዕቃ ለያዙ እንዲያዙ ለተባበሩ እና ድጋፍ ላደረጉ ዋናው ቅጂ ይሰጣል፣ በግልባጭ ለሀብት አስተዳደር፣ ለኦዲትና ኢንስፔክሽን እና ለመረጃ ምርመሪና የሥጋት ሥራ አመራር የሥራ ሂደት ያሳውቃል በሚል ተሻሽሏል፡፡

በነበረው መመሪያ ቁጥር 15/2001 ለያዥ፣ ድጋፍናትብብር ለሚያደርጉ ሰዎች ማስረጃ የሚሰጥበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ አሁን ግን ለያዥ ድጋፍና ትብብር ለሚያደርጉ ማስረጃ ይሰጣቸዋል ለክፍያ ሲቀርቡም ይህንኑ የተሰጣቸውን ኦርጅናል ቅፅ ይዘው ሲቀርቡ የወሮታ ክፍያ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ከፍ ብሎ በአንቀፅ 8/1/ እና 8/5/ በተገለፀው መሠረት፣ ለያዥ ድጋፍናትብብር ላደረጉ ማስረጃ ሲሰጣቸው በወቅቱ ከፍ ብሎ ለተጠቀሱ የሥራ ሂደቶች ግልባጭ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ ይህም ሊፈጠር ይችላል ተብሎ የሚገመተው ክፍተት ለመሸፈን በማሰብ ነው፡፡

**አንቀፅ 14** ***<u>የተያዙ ዕቃዎች አቀማመጥ</u>***

*ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 አልተሻሻሉም*

*ንዑስ አንቀፅ 3  በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ስለተያዘው ሕገወጥ ዕቃ አቀማመጥ አሻሻጥ እና አወጋገድ በተመለከተ በአዋጅ አንቀፅ 31/8/ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል የሚል አዲስ አንቀፅ ተጨምሯል፡፡ ምክንያቱም በቀረጥና ታክስ የማይወገዱ ዕቃዎችን በዚህ አንቀፅ መሠረት በፍጥነት እንዲፈፀሙ እና ለባለመብቶቹ እንዲከፈላቸው ለማድረግ ሲባል ነው፡፡*

**አንቀፅ 15** ***<u>በተያዙ ዕቃዎች ላይ እንዳይፈፀም የተከለከለ ተግባር</u>***

*አልተሻሻለም*

***<u>ክፍል አራት</u>***

***<u>የወሮታ ክፍያ አፈፃፀም</u>***

**አንቀፅ 16** ***<u>መሠረቱ</u>***

*ንዑስ አንቀፅ 1 አልተሻሻለም*

*ንዑስ አንቀፅ 2 የንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ የወሮታ ክፍያ የሚከፈለው ሕገወጡ ዕቃ ለባለሥልጣኑ ገቢ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በ3 ወር ውስጥ በቀረጥና ታክስ ወይም በሽያጭ ወይም በሌላ ማናቸውም ሁኔታ እንዲተላለፍ ወይም እንዲወገድ ቢደረግም ባይደረግም የወሮታ ክፍያ ይፈፀማል የሚል አዲስ አንቀፅ ተጨምሯል፡፡ ይህም የአወጋገድ ሁኔታውን ለማፋጠን፣በየመጋዘኑ በማስቀመጥ ችግር የሚፈጠርበትን ሁኔታ ለማቃለል እንዲሁም ተከፋዮቹም ወደ ተመሳሳይ ተግባራቸው ተሰማርተው ሕገወጥ ዕቃን የመከላከል ተግባራቸውን እንዲወጡ ለማድረግ ነው፡፡*

*ንዑስ አንቀፅ /3/ ቀረጥና ታክስ ሊወጣላቸው ከማይችሉ ሕገወጥ ዕቃዎች በስተቀር የተያዘውን ሕገወጥ ዕቃ ቢሸጥም ወይም ቢተላለፍም ወይም በማናቸውም መንገድ ቢወገድ የወሮታው ክፍያ መሠረት የሚያደረገው በዕቃው ላይ የተከፈለውን ቀረጥና ታክስ ሲሆን መቀጮውን አይጨምርም የሚል አዲስ አንቀፅ ተጨምሯል፡፡ የኮንትሮባንድ እቃንም በተመለከተ በዋነኛነት በኮንትሮባንድ ለገባው ዕቃ ቀረጥና ታክስ ላይ መሠረት ተደርጐ*

ቀረጥና ታክሱ የሚሰብሰብ ሲሆን ቀረጥና ታክስ የማይወጣላቸው በሚሆኑበት ጊዜ በረቂቁ አንቀፅ 18/3/ ላይ በተገለፀው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ንዑስ አንቀፅ 4፣ ባለሥልጣኑ ለጠቋሚ ብቻ ይሰጥ የነበረው ማስረጃ ለያዥም፣ ደጋፊና ተባባሪ እንዲሰጥ በመመሪያው አንቀፅ 8/1/፣ 8/5/፣ 13/3/ የተሰጣቸው ማስረጃ ዋና ቅጂ ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በሚል እንዲጨመር ተደርጓል፡፡

## 17. ሕገወጥ ዕቃ ለባለሥልጣኑ ገቢ ሆኗል ስለሚባልበት ሁኔታ

በአዋጁ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል ሕገወጥ ዕቃ ለባለሥልጣኑ ገቢ እንደተደረገ የሚቆጠረው፡፡

1. አልተሻሻለም
2. ለተያዘው ዕቃ ባለቤት ወይም ኃላፊ የሆነ ሰው ማስታወቂያ በወጣ በ30 ቀናት ውስጥ ካልቀረበ ወይም በዚህ ጊዜ ውስጥ በፍ/ቤት ክስ ካልተመሰረተ በዕቃው ላይ የሚኖረው መብት ተቋርጦ ዕቃው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 31 መሠረት ሲወገድ ወይም፤
3. በሕገወጥ ዕቃ ባለቤት፣ በግብር አበሮቹ እና/ወይም በተባባሪዎች ላይ ባለበትም ሆነ በሌለበት በቀረበባቸው የወንጀል ክስ መሠረት ሥልጣን በተሰጠው ፍ/ቤት በዕቃው ወይም በወንጀለኛው ላይ የመጨረሻ የውርስ ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲሰጥ፣ ወይም
4. ተከሳሹ ፍ/ቤት ባለመቅረቡ ምክንያት ክስ የማቅረብ መብት ተጠብቆ በተዘጋ ክስ ላይ ፍ/ቤት ሕገወጥ ዕቃው ተሽጦ ለባለሥልጣኑ ገቢ እንዲሆን ትዕዛዝ ሲሰጥ ወይም ባለሥልጣኑ ሕገወጥ ዕቃ በአስተዳደራዊ ውሳኔ አስፈላጊውን ክፍያ ተከፍሎ እንዲወጣ ሲወሰን ገቢ ሆኗል ማለት እንደሆነ ከንዑስ አንቀፅ 2 እስከ 4 በዚሁ እንዲሻሻል የተደረገ ሲሆን አዲስ ሀሳብ በንዑስ አንቀፅ 5 ተካቷል ይህም ቀረጥና ታክስ ማሳነስ ወይም ማጭበርበር በተፈፀመበት ሕገወጥ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ ከተሰበሰበ ገቢ ሆኗል የሚል ዕንዲጨመር ተደርጓል፡፡ይህም የሆነበት ምክንያት ቀረጥና ታክስ ከመሰብሰብ ውጭ ገቢ የሚሆን ዕቃ ላይኖር የሚችልበትን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

## 18. የወሮታ ክፍያ መጠን

18/1/ የቀድሞ ንዑስ አንቀፅ /1/ ከሽያጭ ዋጋ የሚለው ተሰርዞ ለወሮታ ክፍያ መሠረት የሚደረገው በማንኛውም መልኩ ሲተላለፍ ባለሥልጣኑ ከሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ላይ እንዲሆን ይህም በቀረጥ ነፃ የገባው ዕቃ በሕገወጥ መንገድ ሲተላለፍ በተላለፈበት ቀን በነበረው ቀረጥና ታክስ ይከፈል ዘንድ ነገር ግን ዕቃው የተላለፈበት ትክክለኛ ጊዜ የሚታወቅ ካልሆነ ዕቃው ወደ ሀገር ውስጥ ገብቷል ተብሎ የሚገመትበትን ጊዜ መሠረት አድርጐ ቀረጥና ታክስ የሚሰበሰብ ሲሆን የወሮታ ክፍያው መሠረት የሚያደርገው ባለሥልጣኑ በየትኛውም ሁኔታ በተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ላይ ነው። እንዲሁም በቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ገብተው በሌላ አገልግሎት ወይም መብት በሌላቸው ግለሰቦች ይዞታ ሥር የተያዘ ዕቃ ይል የነበረው በጊዜያዊነት የገቡ ዕቃዎችንም በተመሳሳይ እንዲካተቱ ተደርጓል። የክፍያ መጠኑ በመቶኛ ከዚህ በታች ቀርቧል።

ሀ/ ለጠቋሚ 15%፣ ለ/ ለያዥ ድጋፍና ትብብር ላደረጉ 10%፣ ሐ/ለክልል ወይም ለከተማ መስተዳድር ወይም ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፌዴራል ፓሊስ 50%፣ መ/ ለህግ አስከባሪው ጥቆማ ያቀረበው ግለሰብ ከሆነ ለሕግ አስከባሪ ከሚከፈለው 50% ላይ 15% በመቀነስ ለጠቋሚው የወሮታ ክፍያ ተፈፃሚ ይደረጋል በሚል ተሻሽሏል።

18/2/ ንዑስ አንቀፅ 2 መከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዳይከፈል ማጭበርበር ወይም ማሳነስ ወይም ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ማድረግ የሚል ተጨምሯል፤

ማንኛውም ሰው መከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንይይከፈል ወይም አሳንሶ ለመክፈል ወይም ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ለማድረግ በማናቸውም ሁኔታ ማጭበርበር ወይም ማሳነስ መፈፀሙ ተጠቁሞ በምርመራ የተገኘ እንደሆነ ማለትም ዕቃው ከጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሳይወጣም ይሁን ከወጣ በኋላ ማጭበርበር እንደተፈፀመበት ከተጠቆመ በተለይም በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያለውና በፍተሻ የታለፈው እንደገና እንዲፈተሽ ወይም ወደ አገር ሲገባ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በማስፈተሽ እንዲሁም ከጉምሩክ ቁጥጥር የወጣ ከሆነም በዕቃው ላይ የተገኘውን የሕገወጡን ዕቃ ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል ሲባል በመመሪያው ተካቷል።

18/3/ ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው የባለሥልጣኑ ሹም ፈቃድ ሳያገኝ አስፈላጊውን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት በመፈፀም ወደውጭ አገር እንዲወጣ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ወይም

እንዲተላለፍ በተፈቀደ ማጓጓዣ ወይም የዕቃ መያዣ ላይ የተደረገውን ማሸጊያ በመፍታት ወይም መያዣውን ከፍቶ ወይም ሰብሮ ዕቃውን ማጉደሉ ጥቆማ ደርሶ የተያዘ እንደሆነ ለጠቋሚ፣ያዥ፣ተባባሪና ደጋፊ እንዲሁም ለክልል ወይም ለከተማ መስተዳድር አካላት ወይም ለመከካያ ሠራዊት ወይም ለፌዴራል ፓሊስ የወሮታ ክፍያ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ይህም አዲስ የተካተተ ሀሳብ ሲሆን የጉምሩክ ህግን በመተላለፍ በህጋዊ መንገድ እንዲወጡ የተፈቀዱ ዕቃዎችን በህገወጥ መንገድ ሀገር ውስጥ እንዲቀሩ በማድረግ ወይም በህጋዊ መንገድ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ቀረጥና ታክስ በአግባቡ እንዳይሰበሰብ ወይም ተገቢ ዕቃ አግባብ ላለው አካል እንዳይደርስ የሚደረግበት ሁኔታ እየተከሰተ በመሆኑ ይህንን የጉምሩክ ወንጀል ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሲባል እንዲካተት ተደርጓል፡፡ የአከፋፈሉን ሁኔታ በተመለከተ ባለሥልጣኑ ሽያጭ ላይ ለማይውሉ ህገወጥ ዕቃዎች ከሚይዘው በጀት ላይ ተፈፃሚ እንዲሆን በማድረግ የተያዘው እቃ ቀረጥና ታክስ ሊሠራለት የሚችል ሲሆን ቀረጥና ታክሱን መሠረት በማድረግ የወሮታ ክፍያው ተፈፃሚ ሲሆን ቀረጥና ታክስ ሊሠራለት የማይችል ሲሆን ደግሞ የተያዘው ህገወጥ ዕቃ ምን ያህል ዋጋ ሊያወጣ ይችላል የሚለውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የወሮታ ክፍያው ተፈፃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

18/5/ ሽያጭ ላይ የማይውሉ ሕገወጥ ዕቃዎች የወሮታ ክፍያ መጠን በመግቢያው የተገለፀው እንዳለ ሆኖ ሌሎች ተጨምረዋል፡፡

1/ የልባሽ ጨርቅ በኪሉ ብር 10.00 ይል የነበረው፣ በኪሎ ለጠቋሚ ብር 25፣ ለያዥ ድጋፍናትብብር ላደረጉ ብር 15፣ ለክልል ወይም ከተማ መስተዳድር ወይም ለፌዴራል ፓሊስ ብር 50 ይከፈላል በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

2/ ሕገወጥ ዕቃዎች በሚመለከተው መሥሪያ ቤት የገበያ ዋጋ የወጣለት ከሆነ የዚሁ ዋጋ ለጠቋሚ 20%፣ ለያዥ፣ ድጋፍናትብብር ላደረጉ 15%፣ ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፌዴራል ፓሊስ ወይም ለክልል ወይም ለከተማ መስተዳድር አካላት 40% እንዲከፈል በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

3/ ሕገወጥ ዕቃው የገበያ ዋጋ ሊወጣለት የማይችል ከሆነ ባለሥልጣኑ በሚሰይመው ከ3 ያላነሱ የቡድን አባላት እንደየዕቃው ባህሪ እየተጣራ በሚሰጡት ዋጋ ላይ ለጠቋሚ 10%፣ ለያዥ፣ድጋፍናትብብር ላደረጉ 5%፣ ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፌዴራል ፓሊስ ወይም ለክልል ወይም ለከተማ መስተዳድር አካላት 30% እንዲከፈል በሚል ተካቷል፡፡

እንደየዕቃው ባህሪ ሲባል የቡድኑ አባላት የተያዘውን ዕቃ አደገኛነት ወይም ለተያዘው ዕቃ እንደሚሰጠው ክብደት ወዘተ ግምት ውስጥ በማስገባት የሚከፈልበት ሁኔታ ነው፡፡

4/ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ተራ ቁጥር /1/፣/2/ እና /3/ አፈፃፀም ለህግ አስከባሪ ጥቆማ ያቀረበው ግለሰብ ከሆነ ከተቋሙ ከሚከፈለው ብር 50፣ 40% 30% ክፍያ ላይ በዚሁ ንዑስ አንቀፅ 5/1/-/3/ እንደቅደም ተከተል ለጠቋሚ የተመለከተው ተቀናሽ ተደርጐ ለጠቋሚ ይከፈለዋል የሚል አዲስ ፊደል /መ/ ተጨምሯል፡፡

18/6/ የተያዘው ሕገወጥ ዕቃ የውጭ ሀገር ገንዘብ በሚመለከት አዲስ አንቀፅ ተጨምሯል፡፡ /ሀ/ ለያዥ 15%፣ /ለ/ ለጠቋሚ 10%፣ /ሐ/ ለትብብርናድጋፍ ላደረጉ 5%፣ /መ/ ዕቃው የተያዘው በሕግ አስከባሪ አካላት ሲሆን 30% ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ ብር ከተመነዘረ በኂላ የወሮታ አበል እንዲከፈል፣ሆኖም የውጭ ሀገር ገንዘብ ሲሆንና የኢትዮጵያ ብር ሲሆን የሚከፈለው ወሮታ ክፍያ መጠን ይለየያል፡፡ የኢትዮጵያ ብር ሲሆን መጠኑ ይጨምራል ይህም የሆነበት ምክንያት የውጭ ገንዘብ ሲመነዘር መጠኑ ከብር ስለሚበልጥ ሁለቱን ለማመጣጠን ሲባል እና በሕገወጥ መንገድ የሚደረገውን የብር ዝውውር ለመግታት እና ጠቋሚዎችም ለሁለቱም ትኩረት እንዲሰጡ ለማድረግ ሲባል ነው፡፡

ሠ/ ለዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ /መ/ አፈፃፀም ለሕግ አስከባሪ ጥቆማ ያቀረበው ግለሰብ ከሆነ ለጠቋሚ ከሚከፈለው 30% ክፍያ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ በፊደል ተራ /ለ/ የተመለከተው ተቀናሽ ተደርጐ ለጠቋሚ ይከፈላል፡፡

18/7/ የተያዘው ሕገወጥ ዕቃ የኢትዮጵያ ብር ከሆነ

ሀ/ ለያዥ 20%

ለ/ ለጠቋሚ 15%

ሐ/ ትብብር እና ድጋፍ ላደረጉ 5%

መ/ ዕቃው የተያዘው በሕግ አስከባሪ ሲሆን 35%

ሠ/ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ ፊደል ተራ /መ/ አፈፃፀም ለሕግ አስከባሪ ጥቆማ ያቀረበው ግለሰብ ከሆነ ለሕግ አስከባሪ ከሚከፈለው 35% ክፍያ ላይ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ /ለ/ የተመለከተው ተቀናሽ ተደርጐ ለጠቋሚው ይከፈላል፡፡

18/8/ ሕገወጡን ዕቃ ለያዙ የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር ወይም የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፌደራል ፓሊስ አባላት እንደየዕቃው ባህሪ በመመሪያው ለያዥ የጠቀሰውን ክፍያ ለህግ አስከባሪው ከሚከፈለው ክፍያ ላይ ተቀንሶ ይከፈላቸዋል የሚል አዲስ ንዑስ አንቀፅ ተጨምሯል፡፡ ይህ እንዲካተት የተደረገው የሕብረተሰቡን እንቅስቃሴ ለማጠናከርና በመከላከሉናበመተግበሩ ዙሪያ ለማነሳሳት እንዲሁም ዕቃውን የሚይዙት መ/ቤቶች ዕቃውን እንዲይዙ ላስማራቸው ሠራተኞቹ ማበረታቻ ይሆን ዘንድ ነው፡፡

18/9/ ሽያጩን ለማከናወን የወጣው ወጪን ከወሮታ ክፍያ ተቀናሽ ስለሚሆንበት፤

የተያዘው ሕገወጥ ዕቃ ሲሸጥ ወይም ቀረጥና ታክስ ተከፍሎ ሲወጣ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ሲወገድ ሽያጩን ለማከናወን የወጣውን ወጪ፣ የመጋዘን ኪራይ እና ዕቃው ለማጓጓዝ የወጣውን ወጪ ከተቀነሰ በኋላ በቀረበው ሂሳብ ላይ የወሮታ ክፍያ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ የሚል አዲስ ንዑስ አንቀፅ ተጨምሯል፡፡ ይህም የሆነው ባለሥልጣኑ በተያዘው ሕገወጥ ዕቃ ምክንያት ሌላ ወጭ እንዳያወጣ ወይም ለሌላ ወጭ እንዳይዳረግ ሲባል ነው፡፡

18/10/ በመመሪያ ቁጥር 15/2001 አንቀፅ 18/4/ የነበረ በዚሁ ንዑስ አንቀፅ 8 እንዲሆን ተደርጓል፡፡

## 19. <u>የወሮታ ክፍያ ፈፃሚ ሊያከናውናቸው የሚገቡ ተግባሮች</u>

የወሮታ ክፍያ ፈፃሚው አካል የወሮታ ክፍያው መፈፀም ባለበት ጊዜ ውስጥ መፈፀም እንዲችል ክፍያው ከመፈፀሙ አስቀድሞ የተለያዩ ማስረጃዎችን የማሰባሰብ ተግባር ሊያከናውን ይገባል፡፡ ይህም የተለያዩ ክፍተቶችን ለመሙላት እና ተደጋጋሚ የክፍያ ጥያቄዎችን ለመቆጣጠር ይረዳል፡፡ በመሆኑም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /1/ እና /2/ የተዘረዘሩት ማስረጃዎች በመሰብሰብ በ3 ወር ጊዜ ወስጥ ክፍያውን ተፈፃሚ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ክፍያው መዘግየት ስለሌለበት እና ተከፋዮቹም እንዳይጉላሉ ወይም ወደሌላ ተመሳሳይ ሥራ ይሰማሩ ዘንድ ለወሮታ ተከፋይ(ጠቋሚ/ያዥ ደጋፊና ተባባሪ) ለሆኑት ሊከፈላቸው እንደሚገባ እና የሀብት አስተዳደር የወጣውን ገንዘብ ዕቃዎቹ የሚወገዱበትነ ሁኔታ እንዲፋጠን በሚል አዲስ አንቀፅ ተጨምሯል፡፡ በተጨማሪም በድህረ ዕቃ አወጣጥ ሥርዓት መሠረት ማሳነስ ወይም ማጭበርበር ድርጊት በሆነ ጊዜ የሀብት አስተዳደር ወይም ፋይናንስ ቀረጥና ታክሱ እንዲሁም መቀጫው ገቢ መሆኑን

እንዲያረጋግጥ በዚሁ አንቀፅ ተጠቅሷል፡፡ ምክንያቱም ማጭበርበር ወይም ማሳሳት የተፈፀመበት ዕቃ ለገበያ ቀርቦ ሊሸጥ የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል የሚያዝና ወደመጋዘን ገቢ የሚደረግ ዕቃ ላይኖር ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ ሳይሆን ቀርቶ ማጭበርበር ወይም ማሳነስ የተፈፀመበት ዕቃ ከተያዘና ወደመጋዘን ገቢ ከተደረገ በንዑስ አንቀፅ /1/ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች እንደ አግባቡ ሁኔታ መረጃ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 20. የወሮታ ክፍያ መብት የሚተላለፍ ስለመሆኑ

የወሮታ ተጠቃሚ በማንኛውም ሁኔታ ቢሞት ቢጠፋ አግባብ ባለው ሕግ የተረጋገጠ ማስረጃ ይዞ ለሚቀርብ የወሮታ አበል ሊከፈል እንደሚገባ አዲስ አንቀፅ ተጨምሯል፡፡

### 21. የይርጋ ጊዜ

ንዑስ አንቀፅ /1/ የመመሪያ ቁጥር 15/2001 አንቀፅ 19 የነበረ ነው አልተሻሻለም

### 22. የመሸጋገሪያ ድንጌጋ

የመመሪያ ቁጥር 15/2001 አንቀፅ 20 የነበረ ነው፤

### 23. የተሻረ መመሪያ

የመመሪያ ቁጥር 15/2001 አንቀፅ 21 የነበረ ነው፤

መመሪያ ቁጥር 15/2001 በዚህ ለቂቅ መመሪያ የተሻረ መሆኑ ተገልጿል፡፡

### 24. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

የመመሪያ ቁጥር 15/2001 አንቀፅ 22 የነበረ ነው፡፡

**NB** ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የወሮታ ክፍያ መጠን መቶኛ ቀደም ሰል ከነበረ ስሌት የተወሰደ ስለሆነ ይህንኑ መቶኛ ሊቀነስ፣ሊጨመር ወይም ሊፀድቅ እንደሚችል እንዲሁም ያልተሻሻሉትን አንቀፆች ቢሆን አይሻሻልም ማለታችን አለመሆኑ በትህትና እናሳስባለን፡፡

# <u>የሕገ ወጥ እቃዎች መረጃ አሰጣጥና የወሮታ አከፋፈል የወጣ መመሪያ ቁጥር 15/2001ን ለማሻሻል ምክንያት የሆነው የመነሻ ሀሳብ</u>

1. <u>መመሪያው የወጣበት ዓላማ</u>
   - የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመቆጣጠር፣ ሕብረተሰቡም እነዚህን ወንጀሎች በሚመለከት ከመንግሥት ጋር በመተባበር ግዴታውን እንዲወጣ መንግሥት ሊያገኘው የማይቻለውን መረጃ በመስጠት ሕገ ወጥነትን ለመከላከል እንዲቻል ለማድረግ፣
   - የጉምሩክን ሕግን በመተላለፍ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በይዘትም በመጠንና በዓይነት እየተበራከቱ በመምጣታቸው በተጠናከረ መልኩ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ስልቶችን መዘርጋት በማስፈለጉ፣
   - በጉምሩክ ሕግ መተላለፍ ወንጀሎችን ለመከላከል አስተዋጾኦ ለሚያደረጉ ጠቋሚዎችና ተባባሪዎች መልካም ተግባራቸው ጋር የተመጣጠነ ወሮታ ሊከፈላቸው የሚገባ በመሆኑ ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 78/3/ መሠረት መመሪያ እንዲያወጣ ሥልጣን በመሰጠቱ፣

2. <u>መረጃን የመስጠት ግዴታ</u>

በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 78/1/ መሠረት “የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ” ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት ወይም ባነስተኛ የተከፈለበት ወይም ኮንትሮባንድ እቃ መኖሩን የሚያወቅ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ “የባለሥልጣኑ ጽ/ቤት” ወይም “የሕግ አስከባሪ አካል” <u>“ማሳወቅ”</u> እንዳለበት እንዲሁም የአዋጅ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተገለፀው መሠረት ለባለሥልጣኑ ወይም ለህግ አስከባሪው አካል በተሰጠ <u>“ማስረጃ”</u> መሠረት የተገኙ እቃዎች በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ለማድረግ ለተባበሩት ድጋፍና መረጃ ለሰጡት ሰዎች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ወሮታ እንደሚከፈል ተደንግጓል።

ከድንጋጌው መረዳት የሚቻለው የሚወጣው መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 78/1/ ጽንሰ ሃሳብ መሠረት በማድረግ መሆኑን ያስረዳል። በዚህ መሠረት የሕገ ወጥ እቃዎች መረጃ አሰጣጥ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 15/2001 ወጥቶ ከግንቦት 1/2001ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚ ሆኗል።

የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰንም በሕገ ወጥ እቃዎች ላይ የሚቀርቡ ጥቆማዎች አቀራረብ <u>"አያያዝ"</u> <u>"የተየዙ እቃዎች"</u> ለባለሥልጣኑ ገቢ ስለሚሆኑበት ሁኔታ እና በወሮታ አከፋፈል ጉዳዩች ተፈፃሚ እንደሚሆን በመመሪያ አንቀጽ 3 ተገልጾል፡፡

3. **የወጣው *መመሪያ* ከእናት ሕጉ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 78/1/ *ጋር* በማገናዘብ "ሕገ ወጥ እቃ ምንና ምን ይሸፍናል" "ጠቋሚ" "ያዥ" እና "ሕግ አስከባሪ" ማነው የመሳሰሉት ጥያቄ ያስነሳል፡፡**

   1. <u>ሕገ ወጥ እቃ ምንና ምን ይሸፋናል?</u>

      በመመሪያው አንቀጽ 2/1/ ሕገ ወጥ እቃ ማለት " የጉምሩክ ሕግን" ወይም <u>"**ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚያስፈጽማቸውን ሕጐች**"</u> በመተላለፍ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት ወይም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ወይም የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ወይም ኮንትሮባንድ እቃ ነው በማለት ተርጉሞታል፡፡ እንዲሁም ከዚሁ አዋጅ አንቀፁ ላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ተቀንሶ የወጣ አለ፡፡ ስለሆነም ይህ ቢስተካከል፡፡

      - የጉምሩክ ሕግ በመተላለፍ ካለ በኋላ የተወሰነቱን የጉምሩክ መተላለፎች ዘርዝሮ "<u>ነው</u>"፡፡ በማለት በመደምደሙ መመሪያው በተዘረዘሩት መተላለፎች ብቻ ተወስኖ እንዲቀር ዝግ አድርጐታል፡፡
      - ሌሎች የጉምሩክ መተላለፍ ወንጀሎች ማካተት ሲገባው አላካተተም፡፡ ነገር ግን "የጉምሩክ ሰነድ ማጭበርበር"፣ "በሕጋዊ እቃ ከለላነት የሚገቡ ሕገ ወጥ እቃዎች"፣ እና ወዘተ እንደሚያካትት በግልጽ አላስቀመጠም፡፡ ነገር ግን <u>የጉምሩክ ሕግን መተላለፍ</u> የሚመለከቱ ሁሉ እንደሚጨምር የሚያከራክረን አይመስለንም፡፡

        እነዚህ ከላይ የአብነት ያክል የጠቀስናቸው የጉምሩክ መተላለፎች በመመሪያው የወሮታ ክፍያ መጠን ዝርዝር ላይ ባይካተቱም በተለያዩ አንቀጾች የወሮታ ክፍያ ተጠቃሚ የሚያደረጉ መሆናቸው ለመረዳት ይቻላል፡፡

   ሀ. በመመሪያ የወሮታ ክፍያ አፈፃፀም ሥር አንቀጽ 16/1/ በጥቆማ ወይም ያለምንም ጥቆማ ሕገ ወጥ እቃ ከተያዘ ጠቋሚው፣ ያዥ፣ ትብብር እና ድጋፍ ያደረጉት በሙሉ የወሮታ ክፍያ እንደሚከፈላቸው እና በንዑስ አንቀጽ /2/ በዚህ መመሪያ

መሠረት የወሮታ ክፍያ የሚከፈለው ለባለሥልጣኑ ገቢ የሆነው ሕገ ወጥ እቃ "በሽያጭ" ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ እንዲተላለፍ ከተደረገ" ወይም እንዲወገድ ከተደረገ ወይም " ለተያዘው እቃ ቀረጥና ታክስ ክፍሎ እንዲወጣ ከተደረገ ክፍያው እንደሚፈፀም ያስረዳል፡፡

ለ. በሌላ በኩል በመመሪያ አንቀጽ 17 መሠረት ሕገ ወጥ እቃ ለባለሥልጣኑ ገቢ ሆናል ስለሚባልበት ሁኔታ ውስጥ፡-

- በሕገ ወጥ እቃ ባለሥልጣኑ በአስተዳደራዊ ውሳኔ አስፈላጊው ክፍያ ተከፍሎ እንዲወጣ ሲወስን፣
- የሕገ ወጥ ዕቃ ባለቤት በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲወረስ ስምምነቱን በፊሪማው በማረጋገጥ እቃው ገቢ ከሆነ ጠቋሚው ወሮታ ክፍያ ተጠቃሚ እንደሚሆን ያስረዳል፡፡

ሐ. በመመሪያ አንቀጽ 16/3/ መሠረት የጠቋሚነት ማስረጃ የተሰጠው ሰው የክፍያ ጥያቄ በሚያቀርብበት ወቅት የማስረጃውን ዋና ቅጅ ይዞ መቅርብ ይኖርበታል በማለት በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ስለሆነም በአንቀጽ 16/1/ እና /2/ መሠረት <u>የጉምሩክ መተላለፎችን</u> መጠቆሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይዞ ሲቀርብ የወሮታ ክፍያ እንደሚከፈል ያስረዳል፡፡

መ. የወሮታ ክፍያ መጠን በሚመለከት በመመሪያው አንቀጽ 18 የወሮታ ክፍያ መጠን ሲዘረዝር በሶስት ደረጃ የተከፈሉ ናቸው፡፡ ይኸውም፡-

1. የተያዘው ሕገ ወጥ እቃ ሲሸጥ፣
2. በቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ገብተው መብት በሌላቸው ግለሰቦች ይዞታና አገልግሎት <u>**"የተያዘ እቃ"**</u>
3. በሽያጭ ላይ በማይውሉ ሕገ ወጥ እቃዎች ብቻ መሆናቸው ያስረዳሉ፡፡

ነገር ግን በመመሪያው አንቀጽ 16 እና 17 የተገለፁት ፍሬ ጉዳዮች በማጣጣም እና በያንዳንዱ የጉምሩክ መተላለፍ ዓይነት ከተለዩ በኋላ የወሮታ ክፍያ መጠን ማካተተ ሲገባ ሁሉንም አላካተተም፡፡ ከእነዚህም፡-

- ሕገ ወጡ እቃ በሌላ ማናቸውም መንገድ እንዲተላለፍ ወይም እንዲወገድ የተደረጉ፣ እና

- ሕገ ወጡ እቃ ቀረጥና ታክስ ከፍለው እንድወጡ የተደረጉት፣

- በሕገ ወጥ እቃ ባለሥልጣኑ በአስተዳደራዊ ውሳኔ አስፈላጊውን ክፍያ ከፍለው እንዲወጡ ውሳኔ ያገኙት፣
    - የሕገ ወጥ እቃ ባለቤት በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲወረስ የተስማሙባቸው በሚመለከተ የወሮታ ክፍያ መጠን ሳይወጣላቸው በዝምታ ታልፏል፡፡ ለምን በዝምታ እንደታለፈ ግልጽ አይደለም፡፡ ነገር ግን አስፈላጊ ሁኔታዎች አሟልቶና ማስረጃውን ይዞ ለሚቀረብ የወሮታ ክፍያ አይከፈልህም የሚባልበት ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡ ሊባልም አይገባም፡፡
    - የተጠቆመው ሕገ ወጥ እቃ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ባለሥልጣኑ ሲወስን ለመ/ቤቱ ገቢ ማስገኙቱን የሚያከራክር አይደለም፡፡ ይህ ገቢ በጠቋሚው የተገኘ በመሆኑ የወሮታ ክፍያ ሊከፈለው ይገባል፡፡

ሠ. በአስተዳደራዊ ውሳኔ አስፈላጊውን ክፍያ ከፍለው እንዲወጡ የተደረጉ ሕገ ወጥ እቃዎች የወሮታ ክፍያው በተጠቆመው እቃ ዋጋ ላይ ብቻ የሚታሰብ ነው ወይስ በእጥፍ በተከፈለው ዋጋና ቅጣት የሚለውን ጥያቄ ቢነሳ መመሪያው መልስ የሚሰጠው አይደለም፡፡ ነገር ግን ሊሆን የሚገባው የወሮታው ክፍያ በተጠቆመው እቃ ዋጋ እንጂ በተከፈለው እጥፍ ዋጋ ሊሆን አይገባም፡፡ ምክንያቱም በእጥፍ የተከፈለው የእቃ ዋጋ ሳይሆን መቀጫ በመሆኑ መቀጫ ደግሞ በቅጣት ለመንግሥት ገቢ ስለሚሆን ሊከፈል የሚገባው ከተጠቆመው እቃ ዋጋ ላይ ብቻ ነው፡፡

ረ. በሌላ በኩል ሊተኩርበት የሚገባው ለዚህ መመሪያ የሕግ ምንጩ ከሆነው አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 78/1/ ጋር ሲገናዘብ በመመሪያው አንቀጽ 2/1/ ሕገ ወጥ እቃ ሲተረጉም "-------ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚያስፈጽማቸው ሕጐች በመተላለፍ" እንደሚጨምር ተገልጿል፡፡ ሆኖም አዋጁ "የጉምሩክ ሕግ መተላለፎችን" የሚመለከት ብቻ ስለሆነ ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚያስፈጽማቸው ሕጐች መተላለፍን አይጨምርም፡፡ ይህ ሀረግ እንዲካተት ቢደረግ እንኳን ሌሎች ባለሥልጣኑ

የሚያስፈፅማቸው ሕጐች ሊሆኑ የሚችሉት በአዋጁ አንቀፅ 78/1/ ላይ የተዘረዘሩት ማለትም፤ የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ ቀረጥ ያልተከፈለበት ወይም ባነስተኛ የተከፈለበት ወይም የኮንትሮባንድ ዕቃ ውጭ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚያስፈፅማቸው ሕጐች ተብሎ የገባው ሀረግ ከላይ ከተዘረዘሩት ውጭ ስለማይሆንና ሌላ የሕግ ትርጉም ሊሰጥ ስለሚችል እንዲሁም በአዋጁ አንቀፅ 78/1/ ላይ የተገለፀ ባለመሆኑ ከአዋጁ ጋር ቅራኔ ስለሚፈጥር ሊስተካከል ይገባል፡፡

2. <u>ጠቋሚ ማን ነው?</u>

በመመሪያ አንቀጽ 2/3/ መሠረት ጠቋሚ ማለት ስለ ሕገ ወጥ እቃዎች እንቅስቃሴ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሕግ አስከባሪው አካል መረጃ የሚያቀርብ ሰው ሲሆን **<u>"የባለሥልጣኑ ሠራተኞች አይጨምርም"</u>** በማለት ተተርጉሟል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 78/1/ ላይ የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ ቀረጥ ያልተከፈለበት ወይም ባነስተኛ የተከፈለበት ወይም የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ወይም የኮንትሮባንድ ዕቃ መኖሩን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኘው የባለሥልጣኑ ጽ/ቤት ወይም ሕግ አስከባሪ አካል ማሳወቅ አለበት በማለት ተደንግጓል፡፡ ከድንጋጌው የምንረዳው ፍሬ ነገር ማንኛውም ሰው የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ሠራተኛ ይሁንም አይሁንም እንዲሁም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸውን አካላት ጨምሮ ሕገወጥ ዕቃ መኖሩን ሲያውቅ መጠቆም እንዳለባቸው ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡

ነገር ግን በመመሪያው ትርጉም ክፍል ማለትም በአንቀፅ 2/3/ ላይ ጠቋሚ ሲተረጐም የባለሥልጣኑን ሠራተኞች እንደማይጨምር ተደንግጓል፡፡

የመመሪያው ሀሳብ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች በጥቆማ አማካኝነት የሚገኘውን የወሮታ ክፍያ እንዳያገኙ ለማድረግ የታሰበ ቢመስልም በአዋጅ የተጣለን ግዴታ በመመሪያ ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ያለመጠቆም መብት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ አዋጁ በግልፅ ያስቀመጠውን ግዴታ በመመሪያ እንደማንሳት ይቆጠራል፡፡ ነግር ግን በሕግ ሀሳብ በአዋጅ የተጣለን ግዴታ በመመሪያ ማንሳት ተገቢነት የለውም፡፡

ስለሆነም በመመሪያ ቁጥር 15/2001 ላይ ለጠቋሚ የተሰጠው ትርጉም ከአዋጁ ድንጋጌ ጋር ስለሚጣረስ የአዋጁን መንፈስ በያዘ መልኩ የወሮታ ክፍያ ይከፈለውም አይከፈለውም መጠቆም እንዳለበት ተገልፆ መመሪያው ቢስተካከል፡፡

- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ 18 እና በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 86 መሠረት የፌዴራል ፖሊስ የጉምሩክና ታክስ ሕጐችን በመተላለፍ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያስችል የፖሊስ ሃይል የማደረጃትና የማሰማራት ሃላፊነት እንዳለበት፣ ሌሎች ሥልጣንና ተግባር እንደለው ይገልፃል፡፡ ሆኖም እንደ ባለሥልጣኑ ሠራተኞች ሁሉ ፓሊስም ተመሳሳይ ሥራ እንደሚሰራ ያመለክታል፡፡ ነገር ግን በመመሪያው **"ጠቋሚ"** የሚለው ሲተረጉም የፌዴራል ፖሊስ የማይጨምር እንደሆነ አልተገለፀም፡፡
- በሌላ በኩል እነዚህ ሕገ ወጥ እቃዎች ወደ ሀገር የሚገቡት የሀገሪቱን ድንበር ጥሰው የሚገቡ ስለሆነ የመከላከያ ሰራዊት ደግም ድንበር የመጠበቅ ግዴታና ሃላፊነት ያለበት በመሆኑ በድንበሩ/በወሰኑ የሚያዙ ሕገ ወጥ እቃዎች ግዴታው በመወጣት ላይ እያለ በመሆኑ የወሮታ ክፍያ ሊሰጠው ይገባል ወይ የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ፓሊስ የተጣለበትን ኃላፊነት እየተወጣመ ቢሆን የበለጠ ለማበረታታትና ሊፈጠሩ ይችላሉ ተብሎ የሚገመቱ ክፍተቶችን ለመድፈን የወሮታ ክፍያው ተፈፃሚ ሊደረግ የሚችልበት ሁኔታ ቢፈጠር፡፡

በአዋጅና በመመሪያ አለመጣጣም/ቅራኔ ሲፈጠር ተፈፃሚ የሚሆነው የበላይ ሕግ መሆኑን ከሕጐች የእርከን ደረጃ መርሆች መረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ መመሪያው አዋጁን ተከትሎ በተጣጣመ መልክ ሊወጣ/ሊስተካከል ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነም አዋጁ ሊሻሻል ይገባል፡፡

3. <u>ያዥ ማንነው?</u>

በመመሪያው ቁጥር 15/2001 አንቀጽ 2/4/ ያዥ ማለት ሕገ ወጥ እቃዎች ይዞ ለባለሥልጣኑ ገቢ ያደረገው ማንኛውም ሰው ወይም ተቋም ነው በማለት ተርጉሞታል፡፡ የባለሥልጣኑ ሠራተኞች ሆነ የፌዴራል ፖሊስ አባላት አይጨምርም

አይልም። ይህም የሚያመለክተው ሕገ ወጥ እቃ "ማንኛውም ሰው ሊይዝ" እንደሚችል ያስረዳል።

በሌላ በኩል በመመሪያው አንቀፅ 13/1/ መሠረት ጥቆማ የቀረበበት ሕገወጥ ዕቃ በባለሥልጣኑ እና በሕግ አስከባሪው ብቻ እንደሚያዙ ያስረዳል።

ከሕግ አስከባሪውና ከባለሥልጣኑ ውጭ በማንኛዋም ሰው የሚያዙ ሕገወጥ ዕቃዎች ዕቃው ሕገወጥ መሆኑና/አለመሆኑ የሚረጋገጥበት ሁኔታ እንዴት እንደሚያስረክብ፣ ለማን እንደሚያስረክብ፣ ማስረጃ ማን እንደሚሰጠው፣ እንዲሁም ሕገወጥ ዕቃ ይዞ የሚቀርብ በቅድምያ መጠቆም አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ጥያቄ መመሪያው ስለማይመልሰው ምላሽ በሚሰጥ መልኩ ቢስተካከል። በሌላም በኩል ዕቃን መያዝ የሚችለው በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው። ምክንያቱም ማንኛውም ሰው ይይዛል ከተባለ ተጠያቂነት በሌለበት መብት የሚጣስበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

4. <u>ተባባሪ እና ድጋፍ ሰጪ እነማን ናቸው?</u>

በመመሪያው አንቀጽ 2/6/ መሠረት ተባባሪና ድጋፍ ሰጪ ማለት ሕገ ወጥ እቃ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲያዝ ለማድረግ የተሳተፈ ማንኛውም ሰው ነው። በማለት ተርጉሞታል።

በመመሪያው አንቀጽ 8/1/ መሠረት ሕገወጥ ዕቃ በመጠቆሙ ለጠቋሚ ማስረጃ እንደሚሰጠው በግልጽ ያስቀምጣል። ተባባሪና ደጋፊ በመጠቆማቸው የወሮታ ክፍያ ሊያገኙ ይችላሉ። ነገር ግን ተባባሪና ደጋፊ ለመተባበራቸው እና ለመደገፋቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃው በማን በምን ሁኔታ እንደሚያገኙ መመሪያው የሚለው ነገር የለውም። የተሰጣቸውን ማስረጃ ይዘው ካልቀረቡ ደግሞ የወሮታ አበል የሚፈፀምበት ሁኔታ ሊኖር እንደማይችል ይታወቃል። ስለዚህ ማስረጃውን እንዴት እንደሚያገኙ በመመሪያው ሊካተት ይገባል።

5. <u>ሕግ አስከባሪ ማንነው?</u>

በመመሪያው አንቀጽ 2/8/ ሕግ አስከባሪ ማለት በሕግ ማስከበር ተግባር ላይ የተሰማራ "የፌዴራል" ወይም "የክልል" መንግሥት አካል የሆነ የታጠቀ ወይም ያልታጠቀ ሃይል ወይም ሰራዊት ነው በማለት ተርጉሞታል። ይህም ማለት የፌዴራል ፖሊስ፣ የክልል ፖሊስ/አ.አ. አስተዳደር ፖሊስ ጨምሮ/፣ የመከላከያ ሠራዊትን እንዲሁም

ለፀጥታ ተግባር የተሰማሩ ያልታጠቁ አካላትንም እንደሚጨምር ነው፡፡ ነገር ግን በመመሪያ አንቀጽ 18/1/ /ሐ/ እና 2/ሐ/ ለክልል መስተዳደር አካላት ወይም ለመከላከያ ሰራዊት ብቻ የወሮታ ክፍያ እንደሚፈፀም ይገልፃል፡፡ ስለዚህ በአንቀጽ 2/8/ ለሕግ አስከባሪ የተሰጠው ትርጉም ፋይዳው ምንድነው? በሌላ በኩል ለክልል መስተዳደር አካላት ሲፈቀድ ከክልሉ ፖሊስ ውጭ ያሉ ሌሎች የመንግሥት አካላት ማለቱ ነው ወይ? በመመሪያው አንቀጽ 18/3/ በሽያጭ የማይውሉ ሕገ ወጥ እቃዎች ላይ የመከላከያና የክልል መስተዳድር ያልተጠቀሱት ለምንድነው? በተጨማሪም በአንቀፅ 1 ላይ የሚያዘው ሕገ ወጥ እቃ በባለሥልጣኑ መ/ቤት ሠራተኞች **<u>"ተሳትፎ"</u>** ከሆነ ለክልል መስተዳደርና ለመከላከያ ሰራዊት የወሮታ ክፍያው ይከፈላቸዋል ወይስ አይከፈላቸውም? የሚሉ ጥያቄዎች ያስነሳል፡፡ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ **<u>"ተሳትፎ ውጭ"</u>** ከሆነ ይከፈላቸዋል ከተባለ፣ የባለሥልጣን መ/ቤቱ ሠራተኛ **<u>"ተሳትፎ ካለበት"</u>** (በAnalogy) አይከፈላቸውም ማለት ነው? መመሪያው ምላሽ አይሰጠውም፡፡ ስለዚህ መመሪያው በዚህ መልኩ ቢሻሻል፡፡

6. **<u>የወጭ ምንዛሬና ብርን በሚመለከት፡-</u>**

በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2/1/ እቃ ማለት ገንዘብን እንደሚጨምር ተተርጉሞዋል፡፡ የውጭ ምንዛሬና የኢትዮጵያ ብር የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ ያለ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ወደ አገር እንደሚገባና እንደሚወጣ በጥቆማና ያለጥቆማ እንደሚያዝ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በመመሪያው በግልፅ ባይጠቀስም ሕገወጥ ብርና ዶላርን በተመለከተ ለሚሰጥ ጥቆማ ወሮታ እንደሚከፈል አዋጁ ለዕቃ የሰጠውን ትርጉም መሠረት በማድረግ ማካተት ይቻላል፡፡ ነገር ግን መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ በመመሪያው አልተካተተም፡፡ ስለዚህ የውጭ ምንዛሬንና ብር በወጪና ገቢ ቁጥጥር የባለሥልጣኑ በመሆኑ በመመሪያው የወሮታ ክፍያ አፈፃፀም ሊካተቱ ይገባል፡፡

4. **<u>ሌሎች ችግሮችን በሚመለከት</u>**

በመመሪያው አንቀጽ 17/3/ " ተከሳሽ ፍ/ቤት ባለመቅረቡ ምክንያት ክስ የማቅረብ መብት ተጠብቆ በተዘጋ ክስ ፍ/ቤቱ ሕገ ወጥ እቃው ተሸጦ ለባለሥልጣኑ ገቢ እንደሆነ ይቆጠራል" ይላል፡፡

ይሁን እንጂ ክስ የማቅረብ መብት ተጠብቆ የተዘጋ የሚለው አባባል የመጨረሻ ውሳኔ አለማግኘቱን ያመለክታል፡፡ የመጨረሻ ውሰኔ ሳያርፍበት እና ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 31/2/ እና የመመሪያ አንቀጽ 18 መሠረት የማይወገዱ እቃዎች እንደ ገቢ ሳይሆኑ በአደራ/በዲፖዚት እንደተቀመጡ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ይህ ከሆነ ዘንድ በፍ/ቤት ውሳኔ ሳይሰጥበት የሚሸጡ እቃዎች የወሮታ አበል ሊከፈል እንደማይገባ ከአዋጁ ድንጋጌና መመሪያ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ውጤቱን ላልተፈለገ ኪሳራ ይዳርገዋል፡፡ ነገር ግን ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት አይከፈልም የሚለውን ብንከተል መረጃ የሚሰጡ እና ያገኙ የሚጐዱ ይሆናሉ፡፡ በዚህ መሠረት ሁለቱ የሚጣጣምበት ሁኔታ ቢፈለግ፣

በአጠቃላይ በመመሪያ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች አግባብ ካላቸው የአዋጅና ደንብ ድንጋጌዎች ሲታዩ ያለመጣጣም ይታይባቸዋል፡፡ ለአብነት በመመሪያው አንቀጽ 2/5/ "ለሠራተኛ" የተሰጠው ትርጓሜ በባለሥልጣኑ መ/ቤት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሰራ ነው ይላል፡፡

- ነገር ግን ከአዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ 19/1/ /ለ/ መሠረት የወጣው ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀፅ 2/2/ መሠረት ዋና ዳይሬክተር፣ ም/ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና ጊዜያዊ ሠራተኛ "እንደ ሠራተኛ" እንደማይቆጥራቸው፤
- እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2/47/ በጊዜያዊነት ይሁን በቋዋሚነት፣ ሠራተኛ ይሁን ሃላፊ፣ እና ዐቃቤ ሕግ ይሁን መርማሪ እንደሚጨምር ያመለክታል፡፡
- በመመሪያው 15/2001 አንቀጽ 2/5/ በጊዜያዊነት ይሁን በቋዋሚነት ተቀጥረው የሚሰሩት ሠራተኞች መሆናቸው ያስረዳሉ፡፡

  ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ባለሥልጣኑ በቀጥታ ራሱ በሚያስፈጽማቸው የተለያዩ የሕግ ማእቀፎች ለሠራተኛ የተሰጠው ትርጓሜ የተለያዩ መሆናቸው ያስረዳሉ፡፡

ስለዚህ በመመሪያው ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ቃላት ሲኖሩ በአዋጅ/ደንቡ የተሰጠው ትርጓሜ ይሆናል ቢባል፣ ከተሰጡት ትርጓሜዎች ውጭ የሚተረጉም ቃላት ካጋጠሙ ከሌሎች ሕጐች በማገናዘብ እንዲተረጐም ቢደረግ፣

ባለሥልጣኑ ወይም ሕግ አስከባሪው በመመሪያው አንቀፅ 2/3/ እና /6/ መሠረት መረጃ እንደሚቀበሉ፣ በመመሪያው አንቀፅ 13/1/ መሠረት የተጠቆመው ሕገወጥ ዕቃ እንደሚይዙ በግልፅ ያስረዳል፡፡

በሌላ በኩል በአንቀፅ 7 የጥቆማ አቀራረብ፣ በመመሪያው አንቀፅ 9 የጥቆማው ምስጢራዊነት አጠባበቅ፣ በአንቀፅ 10 የጥቆማ ምስጢር መለያ አሰጣጥ፣ በአንቀፅ 11 የጥቆማ ቅፅ ይዘት አቀማመጥና ስርጭት፣ እና በአንቀፅ 12 ስለጠቋሚዎች ይዘት አቀማመጥና ስርጭት፣ እና በአንቀፅ 12 ስለጠቋሚዎች አመላመል በሚመለከት ባለሥልጣኑ እንዴት እንደሚተገብረው በዝርዝር ሲያስቀምጥ ሕግ አስከባሪው በነዚህ ጉዳዮች እንዴት እንደሚተገብረው መመሪያው የሚገልፀው ነገር የለም፡፡

ስለዚህ ጥቆማ መቀበልና መያዝ ለባለሥልጣኑ እና ለሕግ አስከባሪ ከተሰጠ ከላይ የተጠቀሱትን በሚመለከት ሕግ አስከባሪውን አይመለከተውም ማለት ነውን? አይመለከተውም ከተባለ የማይመለከተው ለመሆኑ የሥልጣኑ ወሰን እስከምን ድረስ እንደሆነ በመመሪያው ሊገለፅ ይገባል፡፡

በመመሪያው አንቀፅ 18 የወሮታ ክፍያ መጠን ንዑስ አንቀፅ 1 እስከ 3 የተዘረዘሩት ደረጃዎች የክፍያ መጠኑ በመቶኛ /%/ የተወሰነውን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 31 /1/፣ /5/፣ እና /6/ መሠረት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር የተደረጉት ዕቃዎች የማስወገጃ ወጪ እና/ወይም ሌሎች ታሳቢ ወጪዎች ከተቀነሰ በኋላ ነው ወይስ ሳይቀነስ የወሮታ ክፍያው የሚሰጠው የሚለውን መመሪያው መልስ አይሰጠውም፣

በመመሪያው አንቀፅ 13/2/ መሠረት ሕገወጡ ዕቃ በሕግ አስከባሪ የተያዘ እንደሆነ ተመዝግቦ በ24 ሰዓት ለባለሥልጣኑ እንደሚያስረክብ በንዑስ አንቀፅ /3/ መሠረት በባለሥልጣኑ የተያዙትን ዕቃዎች በጥንቃቄ መዝግቦ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል እንደሚያስረክብ ያስረዳል፡፡ በዚህ ዓይነት ሕገወጥ ዕቃዎቹ ማንም ይያዘው ባለሥልጣኑ ተረክቦ በቁጥጥር ሥር ያደርገዋል ማለት ነው፡፡ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር የዋሉ ዕቃዎች አወጋገድ በሚመለከት በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 31 መሠረት ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል፡፡

ስለዚህ የተያዙ ሕገወጥ ዕቃዎች የወሮታ ክፍያ መጠን ሊፈፀም የሚገባው በአዋጅ አንቀፅ 31 ድንጋጌ መሠረት ዕቃዎቹ በቅድምያ እንዲዋገዱ ከተደረገ በኋላ ወሮታ ሊከፈል ይገባል፡፡

በመመሪያ አንቀፅ 18 የወሮታ ክፍያ መጠን "ለጠቋሚና" "ለያዥ" "ድጋፍ ትብብር ለሚያደርጉ" በማለት በሦስት መደብ የተከፈሉ መሆናቸው ለመረዳት ይችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ጠቋሚና ያዥ ወይም ጠቋሚና ደጋፊ፣ ተባባሪ ወይም ያዥ፣ ደጋፊና ተባባሪ ሆኖ ሲገኝ ሁለቱም ጥቅም/ክፍያ ነው የሚከፈለው ወይስ አንድን ብቻ የሚለው ጥያቄ ቢነሳ መመሪያው ምላሽ ስለማይሰጠው በሚሻሻለው መመሪያ ሊካተት ይገባል፡፡

በመመሪያው አንቀፅ 18/3/ መሠረት "በሽያጭ ላይ የማይውሉ ሕገወጥ ዕቃዎችን በመዘርዘር የወሮታ ከፍያ ለተጠቃሚዎች እንደሚፈፀም ያስረዳል፡፡

ነገር ግን ለሽያጭ የማይውሉ ሕገወጥ ዕቃዎች ዝርዝር እነዚህ ብቻ ናቸው ወይ፣ የዕቃዎቹ አወጋገድ በምን ሁኔታ እና በማን/በእነማን ሲያረጋግጡ ክፍያው የሚፈፀመው የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ይህ ጥያቄ ሊነሳ የሚችለው ሕገወጡ ዕቃ ካልተወገደ ለተደጋጋሚ የወሮታ ክፍያ ሊዳርግ ስለሚችል አፈፃፀምም የሚያስወግድና ክፍያ የሚፈፀም የሥራ ክፍል የተለያዩ እንዲሆኑ በማድረግ መወገድ የሚያረጋግጡ በኮሚቴ /በሌላ ሁኔታ ክፍተቱን በሚያሟላ መልክ መመሪያው ሊሻሻል ይገባል፡፡

4.7. በመመሪያው አንቀፅ 18/2/ ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ገብተው መብቱ በሌላቸው ግለሰቦች ይዞታ ሥር የተያዘን ዕቃ በተመለከተ የሚከፈለው የወሮታ መጠን ለዕቃው ከተከፈለው ቀረጥ ታክስ መሠረት በየደረጃው እንደሚከፈላቸው የሚገልጽ ቢሆንም፣ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ለመንግሥታዊ ተቋማት የተላለፉት መኪናዎች በሚመለከት መመሪያው የሚለው ነገር የለም፡፡ ይከፈለው ቢባል እንኳ ዕቃው በገባበት ጊዜ በነበረው ዋጋ ታሪፍ ነው ወይስ ዕቃው በተላከበት ጊዜ የሚለው ጥያቄ ያስነሳል፡፡

4.8በተጭበረበረ ሰነድ /ፎርጂድ/ ሲንቀሳቀስ የተያዘ መኪኖች የወሮታ ክፍያ መጠኑ በቀረጥ ነፃ መብት ወደ አገር ውስጥ የገቡና መብት በሌላቸው ሰዎች ይዞታ ሥር የተገኘ እኩል ሊሆን ይገባል ወይ እነዚህ በተጭበረበረ ሰነድ እና በቀረጥ ነፃ መብት ገብተው በሌላ ይዞታ በመዋላቸው ተይዘው ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ለመንግሥት መ/ቤቶች የተሰጡትን የወሮታ ክፍያ መጠን ምን ያህል እንደሆነ በመመሪያው የሚሸፈን አይደለም፡፡ በመመሪያው ይሸፈን ቢባል ቢከፈል ኖሮ /cost benefit/ በገባበት ወይስ በተላለፈበት ጊዜ ነው? ወይም በሽያጭ ላይ የማይውሉ ዕቃዎች የወሮታ ክፍያው በየትኛው ቢካተቱ ነው የሚሻለው?

4.9 የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 78 ድንጋጌ ርእስ እንደሚያመለክተው **"መረጃ የመስጠት ግዴታ/Obligation to provide information"** ይላል፡፡ ነገር ግን በአዋጁ አንቀጽ 78/3/አማርኛው **"ማስረጃ"** የሚል ሲሆን እንግሊዝኛው ደግሞ Evidence ሳይሆን information የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ከድንጋጌው ርእስ ለመረዳት እንደሚቻለው በአማርኛው ማስረጃ የተባለው በመረጃ ሊተካ ይገባል፡፡ ይህም አዋጅ በሚሻሻልበት ጊዜ ትኩረት ተሰጥቶት ሊታረም ይገባል እያልን ይህን ማብራሪያ እያቀረብን ይበልጥ በውይይት እንደሚዳብር እምነታችን መሆኑን እንገልፃለን፡፡